አዲስ ዘመን
ኢፕድ
ዓርብ
82ኛ ዓመት ቁጥር 055 ጥቅምት 25 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ
ኃ/የተ/የግል ማህበር

በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም
- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72
ፋክስ፡- 0111 26 23 45 እና
0111 26 23 18
ይዘዙን
ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።
ነገን ዛሬ እንሥራ



# ጀግኖች ኢትዮጵያውያን በመሬት ላይ ያስገኙት ድል በሰላም ውይይቱም ተደግሟል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች በመሬት ላይ ያስገኙትን ታሪካዊ ድል በደቡብ አፍሪካ በነበረው የሰላም ውይይት ዳግም የሚያስረግጥ የሰላም ድል ማግኘት ተችሏል ሲሉ የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡ በድርድሩ ኢትዮጵያ ያቀረበችው ሃሳብ 100 በመቶ ተቀባይነት ማግኘቱንም ተናግረዋል፡፡

የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ከጋሞ ዞን አርባ ምንጭ ከተማ ባስተላለፉት መልዕክት እንደገለጹት፤ የዛሬ ሁለት ዓመት ባልተገባ መንገድ ከወንድሞቻችን እጅግ አሳዛኝ ጥቃት ተሰንዝሮብን ነበር፤ የኢትዮጵያ ልጆች በገዛ ወንድሞቻቸው ባልተገባ ሁኔታ በተኙበት ታርደው፣ ተገድለው፣ ተገፍተው ነበር፡፡

ይህ ሁኔታ ሁላችንንም ያስቆጣ፤ በኢትዮጵያ ሉአላዊነት እና አንድነት ለመጣ ሁሉ ግንባራችንን ለአረር ለመስጠት ዝግጁ መሆናችንን ለኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ያሳየንበት ነበር ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ኢትዮጵያ የምትፈልገው ሰላምና ብልፅግና እንጂ ጦርነት እንዳልነበር አንስተዋል፡፡

ሆኖም እስካሁን ቀጥሎ የቆየውን ጦርነት በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት መንግሥት የተለያዩ ጥረቶችን ሲያደርግ መቆየቱን

ጀግኖች ኢትዮጵያውያን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



አብርሃም በላይ (ዶ/ር)

# ሕዝብ ኀዘንና ቁስሉን እንዲያስብ ሳይሆን እንዲያክም በትዕግስት መሥራት ይጠይቃል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- ችግር በነበረባቸው አካባቢዎች ያለው ሕዝባችን ኀዘንና ቁስሉን እንዲያስብ ሳይሆን እንዲያክም ሰፊ የእፎይታና የጥሞና ጊዜ እንዲያገኝ በትዕግስት መሥራት ይጠይቀናል ሲሉ የመከላከያ ሚኒስትር አብርሃም በላይ (ዶ/ር) ተናገሩ።

ከጥቅምት 24ቱ ጥቃት ትምህርት ወስደን ሁሌም የታጠቅንና የተዘጋጀን መሆናችንን እንደሠራዊት ማረጋገጥ ቀዳሚ ተግባራችን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በትናንትናው ዕለት «ጥቅምት 24 ቀን መቼም አንረሳውም» በሚል መሪ ሃሳብ በመከላከያ ጠቅላይ

ሕዝብ ኀዘንና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# አድርቃይ፣ ኮረምና አላማጣ አካባቢዎች ዳግም የሞባይልና የስልክ አገልግሎት አገኙ

**ጌትነት ምህረቴ**

አዳማ፡- በሰሜን ኢትዮጵያ በጦርነቱ ምክንያት የቴሌኮም አገልግሎት ተቋርጦባቸው በቆዩ አካባቢዎች ባለፉት ቀናት በተሠሩ የጥገና ሥራዎች አድርቃይ፣ ኮረምና አላማጣ አካባቢዎች ዳግም የሞባይልና የስልክ አገልግሎት ማግኘታቸውን ኢትዮ ቴሌኮም አስታወቀ።

የኢትዮ ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይዘሪት ፍሬህይወት ታምሩ እንደገለጹት፤ ኢትዮ ቴሌኮም የጥገና ሥራውን ባከናወነባቸው ቆቦ፣ ሮቢት፣ ጎብዬ፣ ዋጃና ዞብል አካባቢዎች የቴሌኮም አገልግሎቶች ዳግም መስጠት ከጀመረ ሁለት ሳምታት ተቆጥረዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም የጥገና ሥራውን በማስፋፋት በተጨማሪነት አድርቃይ፣ አላማጣና ኮረም አካባቢዎች ከትናንት በስቲያ ጀምሮ የስልክ አገልግሎት እንዲያገኙ መደረጉን አስታውቀዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች የቴሌ መሠረተ ልማቶችን መልሶ የመጠገንና የተበላሹ ቴሌኮም ዕቃዎችን የመተካት ሥራ መቀጠሉን የገለጹት ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ፤ በቀጣይ ጊዜያትም ተጨማሪ ከተሞች የቴሌኮም አገልግሎቶቹን ዳግም እንዲያገኙ እንደሚደረግ ገልጸዋል።

ኢትዮ ቴሌኮም በሰሜን ኢትዮጵያ ጉዳት የደረሰባቸው የቴሌኮም መሠረተ ልማቶችን በመጠገን ኅብረተሰቡን ዳግም የቴሌኮም አገልግሎት ተጠቃሚ ለማድረግ ቀደም ሲል የጀመረውን ሥራ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ የተካሄደው ጦርነት በመሠረተ ልማቶች ላይ ከፍተኛ ጉዳትና ውድመት ማድረሱ ይታወሳል።

ፎቶ፡ በሃዱሽ አብርሃ



# ጉባዔው የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን ለማጠናከር እንደሚሠራ አስታወቀ

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ በጦርነቱ ምክንያት የተፈጠረውን ችግር ለማቃለል የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን ለማጠናከር እንደሚሠራ አስታወቀ። የሰላም ስምምነቱ በተሟላ ሁኔታና ያለምንም እንከን እንዲተገበር ማሳሰቢያዎችንና ምክሮችን አቅርቧል።

የኢትዮጵያ ሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ ዋና ጸሐፊ ሊቀ ትጉሀን ቀሲስ ታጋይ ታደለ በትናንትናው ዕለት የአገሪቱን ወቅታዊ ሁኔታ አስመልክቶ የጉባዔው የበላይ ጠባቂ አባቶች በተገኙበት በሰጡት መግለጫ፣ ጉባዔው በጦርነቱ ምክንያት የተዳከመውን የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነት ለማጠናከር በትኩረት እንደሚሠራ አስታውቀዋል።

በጉባዔው አስተባባሪነት ለመላው የአገራችን ሕዝቦች ወደ ሰላም እንዲመጡ አባቶች የፀሎት፣ የምህላና የዱዓ ጥሪ ማቅረባቸው ይታወሳል ያሉት ዋና ጸሐፊው፤ ችግሩ ከመከሰቱ በፊትም ሆነ ከተከሰተ በኋላ ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት የሃይማኖት አባቶች በተደጋጋሚ ቦታውን በመጎብኘት እንዲሁም በጸሎት ሲደክሙ መቆየታቸውን አስታውሰዋል።

ዋና ጸሐፊው፤ የሆነው ሁሉ ከመሆኑ በፊት ችግሩ በሰላማዊ ውይይት እንዲፈታም ከፍተኛ ጥረት ሲያደርጉ የነበረ መሆኑን አንስተው የጊዜያዊ ተኩስ ማቆምም በመፍረሱ ጦርነቱ ዳግም ሲያገረሽም «የሰላም ቅድመ ሁኔታው ሰላም ብቻ ነው» በሚል ርዕስ ዳግም

ጉባዔው የሕዝብ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



# ዘላቂ ሰላምና እድገትን ለማረጋገጥ ስጦርነት መንስኤ የሚሆኑ አስተሳሰቦች እንዳይስፋፉ ማረቅ ያስፈልጋል

ገጽ 2






በአዲስ አበባ ከተማ የመታወቂያ እድሳት አገልግሎት ሊጀመር ነው

ገጽ 2

# «ሪፎርሙ የዳኝነት ነፃነት፣ ገለልተኝነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት»

### - የሕግ ፍትህና የዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

**ገመቹ ከድር**

አዲስ አበባ፡- የዳኞችን ነፃነት፣ ገለልተኝነትና ተጠያቂነት ለማረጋገጥ የፍርድ ቤቶች ሪፎርም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስታወቀ፡፡



ቋሚ ኮሚቴው የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፣ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና የፌዴራል ሸርዓ ፍርድ ቤትን ዝርዝር ዕቅዶችና የአንደኛ ሩብ ዓመት አፈጻጸም ከትናንት በስቲያ ገምግሟል፡፡

በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሕግ ፍትህና ዴሞክራሲ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ወይዘሮ እፀገነት መንግሥቱ በግምገማው ወቅት እንደተናገሩት፣ ለውጤታማ ዳኝነት አገልግሎት በሪፎርሙ የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ሊቀጥሉ ይገባል፡፡

ሁሉም ፍርድ ቤቶች ዕቅዶቻቸውን የአስር ዓመት እቅድን መሠረት በማድረግ በዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደር እና ለፍትህ ሥርዓቱ ውጤታማነት ልዩ ትኩረት በሚፈልጉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡

ቋሚ ኮሚቴው በሪፎርሙ የተገኙ ጠንካራ ጎኖችን አጠናክሮ በማስቀጠል በተስተዋሉ ውስንነቶች ዙሪያ ለማሻሻል የሚያስችሉ ግብረመልሶችን ለሁሉም ፍርድቤቶች በመስጠት ውይይት ተካሂዷል፡፡

የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት መዓዛ አሸናፊ በፍትህ ዘርፉ በሪፎርሙ ለተገልጋዩ ቀልጣፋ አገልግሎት፣ ጥራት ያለው አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ የዳኞች ነፃነት ገለልተኝነትና ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ፍርድ ቤቱ ጥረት አድርጓል ብለዋል፡፡

አገር ማለት ሥርዓት ነው ያሉት ወይዘሮ መዓዛ፤ ፍርድ ቤቱ እስከ አሁን ድረስ የተመዘገቡ ጠንካራ ሥራዎችን በማስቀጠል ከምክር ቤቱ የተሰጡ ግብረመልሶችን ተግባራዊ እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ብርሃነመስቀል ዋጋሪ በበኩላቸው የ2015 ዓ.ም የፍርድ ቤቱን ዝርዝር እቅድና የሩብ ዓመት ሥራ አፈጻጸም ለቋሚ ኮሚቴው አብራርተዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ መሪ እቅዶችን መሠረት በማድረግ የዳኞችን ተጠያቂነት፣ የዳኝነት አገልግሎት ማሻሻል፣ መመሪያዎችን መተግበር፣ በክልሎች ተዘዋዋሪ ችሎቶችን ማጠናከርና በካፒታል ፕሮጀክት የፍርድ ቤቱን ሕንፃ ግንባታ ለማከወን እንደሚሠራ ገልጸዋል፡፡

የዳኝነት አገልግሎትን ሕጉ በሚፈቅደው ተግባራዊ ማድረግ ነው ያሉት ፕሬዚዳንቱ ለዚህም ሪፎርሙን መሠረት በማድረግ የዳኝነት ነፃነት፣ ገለልተኝነትና ተጠያቂነት ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራበት ነው ብለዋል፡፡

የዳኞች ተጠያቂነትን እውን ለማድረግ የዳኞች ሥነ ምግባር ደንብ መዘጋጀቱን ገልጸው በአንደኛ ሩብ ዓመት ሥራ አፈጻጸም ለ5000 ክስ መዝገቦች እልባት ለመስጠት ታቅዶ ለ5881 መዝገቦች እልባት ተሰጥቷል ብለዋል፡፡

እቅዱ ከመቶ ፐርሰንት በላይ ተግባራዊ መደረጉን ጠቁመው፣ በቋሚ ኮሚቴው የተሰጡ ግብረመልሶችን እንደግብዓት በመውሰድ ተግባራዊ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል፡፡ ፍርድ ቤቱ የዳኝነት አገልግሎት የሚሰጥበት ሕንፃ ለመገንባት በተመደበው በጀት መሠረት ቋሚ ኮሚቴው አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግላቸውም ጥሪ አቅርበዋል፡፡

የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ፉአድ ኪያር በበኩላቸው የፍርድ ቤቱን ዝርዝር እቅድና አንደኛ ሩብ አመት ሥራ አፈጻጸም ለኮሚቴው ሲያቀርቡ እንደተናገሩት፣ የበጀት ዓመቱ እቅዶች በተገባደደው በጀት ዓመት የተስተዋሉ ጠንካራና ውስንነቶችን መሠረት በማድረግ ተዘጋጅቷል፡፡

በዋናነት የአገልግሎት ጥራት ተደራሽነት፣ የዳኝነት ነፃነትና የዳኞች ተጠያቂነትን መሠረት በማድረግ የፍትህ አገልግሎቶችን ለማሻሻል ፍርድ ቤቱ አቅዶ እየተሠራበት መሆኑን የገለጹ አቶ ፉአድ፤ ባለፉት ሦስት ወራት ተጠያቂነትን ለማረጋገጥ ከሕግ ውጪ ሲንቀሳቀሱ በተገኙ አራት ዳኞች ላይ እርምጃ መወሰዱን ገልጸዋል፡፡

ፍርድ ቤቱ በአንደኛው ሩብ ዓመት ለ104 ሺህ ክስ መዛግብቶች እልባት ለመስጠት አቅዶ ለ115 ሺህ መዛግብት እልባት መስጠት መቻሉን ገልጸው በቋሚ ምክር ቤቱ የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊ በማድረግ ፍትህ ሥርዓቱን ለማሻሻል ይሠራል ብለዋል፡፡

የፌዴራል ሸርዓ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሼህ ሙባረክ መሐመድ አወል በበኩላቸው የፍርድ ቤቱን የ2015 አንደኛ ሩብ ዓመት ሥራ አፈጻጸም ሪፖርት ለምክር ቤቱ ያቀረቡ ሲሆን፣ ቋሚ ኮሚቴው ፍርድ ቤቱ በተለይ በሕፃናት ማቆያ ዙሪያ ትኩረት እንዲሰጥ አሳስቧል፡፡ ፍርድ ቤቱም በቋሚ ኮሚቴው የተሰጡ አስተያየቶችን ተግባራዊ ለማድረግ እንደሚሠራ ፕሬዚዳንቱ ገልጸዋል፡፡

## በአዲስ አበባ ከተማ የመታወቂያ እድሳት አገልግሎት ሊጀመር ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አቶ ጥራቱ በየነ

አዲስ አበባ፡- በአዲስ አበባ ከተማ የመታወቂያ እድሳት አገልግሎት ከኅዳር አንድ ቀን 2015 ጀምሮ በሁሉም ክፍለ ከተሞች እንደሚጀመር በምክትል ከንቲባ ማዕረግ የአዲስ አበባ ከተማ ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ጥራቱ በየነ አስታወቁ።

የ ከ ተ ማ አስተዳደሩ በወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ላይ እያካሄደ ያለው ሪፎርም እንዲሳካ ባለድርሻ አካላት ሚናቸውን እንዲወጡ አቅጣጫ በተቀመጠበት መድረክ ላይ በመጪው ሳምንት ለሚጀመረው የመታወቂያ እድሳት በየደረጃው ያለው መዋቅር አስፈላጊውን ቅድመ ዝግጅት እያጠናቀቀ መሆኑን ገልፀዋል።

በሁሉም ደረጃ የሚገኙ የአገልግሎት መስጫ ማዕከላት ቀደም ተብሎ በተከናወነው የቅድመ ዝግጅት ተግባርና አሠራሩ መሠረት አገልግሎት ፈላጊውን ኅብረተሰብ በቀናነትና በቅልጥፍና ማስተናገድ እንደሚገባቸውም አሳስበዋል።

በዚሁ መድረክ ላይ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ ሪፎርም ማካሄድ ያስፈለገው ተቋሙ ያጋጠመው ችግር የመልካም አስተዳደር ብቻ ሳይሆን የሀብትና የአገር ደህንነት ስጋት ጭምር በመሆኑ ነው ያሉት አቶ ጥራቱ በየነ ችግሩን በውል ተረድቶ ለመፍትሔው በሚካሄደው ሪፎርም ሁሉም የበኩሉን አስተዋፅኦ መወጣት እንዳለበትም አስገንዝበዋል።

የከተማ አስተዳደሩ የወሳኝ ኩነት ምዝገባና መረጃ ኤጀንሲ በአደረጃጀት፣ በሰው ኃይል፣ በቴክኖሎጂና በግብአት አሠራሩን በማዘመን ቀልጣፋና ውጤታማ አገልግሎት ለመስጠት እያካሄደ ላለው ወሳኝ ሪፎርም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ያላሰለሰ ድጋፍና ትብብር በማድረግ ኃላፊነታቸውን ሊወጡ እንደሚገባም መግለጻቸውን ከከንቲባ ጽ/ቤት የተገኘ መረጃ ያመለክታል።

## ዘላቂ ሰላምና እድገትን ለማረጋገጥ ለጦርነት መንስኤ የሚሆኑ አስተሳሰቦች እንዳይስፋፉ ማረቅ ያስፈልጋል

**ጌትነት ተስፋማርያም**

አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላምና ቀጣይነት ያለው እድገትን ለማረጋገጥ ችግሮችን ሁሉ በጦርነት እና በጉልበት እንፈታለን የሚሉ የርዕዮተ ዓለም አስተሳሰቦች እንዳይስፋፋ በሕግ፣ በትምህርትና በተለያዩ ዘርፎች ማረቅ ይገባል ሲሉ የሕግ ባለሙያው አቶ ዚያድ ሬድዋን ተናገሩ።

ጠበቃና የሕግ አማካሪው አቶ ዚያድ ሬድዋን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በአገራችን አንዳንድ የፖለቲካ ኃይሎች የሚያራምዷቸው የፖለቲካ አካሄዶች ችግሮችን ሁሉ በጦርነት እና በጉልበት እንፈታለን የሚል ግትር አቋም ያለው ርዕዮተዓለምን የያዘ ነው፡፡

እንዲህ ዓይነት አስተሳሰቦች ደግሞ ለጥፋት የሚጋብዙ በመሆናቸው በሕግ ከማገድ ባለፈ በትምህርት ዘርፉ፣ በታሪክና በስነልቦና ይዘቶችም አስተሳሰቡ እንዳይስፋፋ ማድረግ ይገባል፡፡

ለአብነት የአሸባሪው ሕወሓት አስተም ህሮቶቹና አስተሳሰቡም ጽንፍ የወጣ ነው ያሉት አቶ ዚያድ፤ አስተሳሰቡ እኔ የበላይ ነኝ፤ እኔ ብቻ መምራት አለብኝ፤ ሌላው ደካማ ነው፤ በጦርነትም አይችለኝም። ሌላውን እየጨፈለኩ ስልጣንም በጦርነት መያዝ አለብኝ የሚል አስተሳሰብ ያለው ቡድን ነው ብለዋል።

ቡድኑ በግልጽ በማኒፌስቶው ላይ በመጻፍ ወጣቱን ትውልድ ከሰላማዊ ሕይወት ይልቅ ለግጭትና ለብጥብጥ የሚጋብዝ ነው ያሉት አቶ ዚያድ፤ ለግማሽ ምዕተ ዓመት ይህን አስተሳሰቡን ሲያሰርጽ መቆየቱንም ጠቁመዋል።

እንደ አቶ ዚያድ፤ ጽንፈኝነት፣ ጦርነትን፣ ኃይልን መሠረት አድርጎ የበላይ ነኝ የሚል ትርክት መፍጠር፤ በዚህም ንጹሃንን ለጦርነት መጋበዝ የቡድኑ ባህሪ ነው። ይህን አስተሳሰቡን፣ በፕሮፓጋንዳ፣ ሥነጽሑፍ፣ በመገናኛ ብዙኃንና በተለያየ መንገድ በትግራይ አካባቢዎች ሲያሰርጽ ኖሯል። በዘፈኖቹም በየጊዜው ስለጦርነት ነው የሚሰብከው ብለዋል፡፡



አቶ ዚያድ ሬድዋን

አስተሳሰብ ደግሞ ካልታረቀ ወደጦርነትና ዕልቂት እንደሚያመራ የተለያዩ አገራትንም ተሞክሮ ማየት ይቻላል። ናዚ የእኔ ብቻ ምርጥ ነው ፤ አሪያን የተባለው ጎሳ ከሁሉም ይለያል በሚል አስተሳሰብ አይሁዶች ላይ ልዩ ጥላቻን በመቅረጽ በርካቶች ላይ ጭፍጨፋ አድርሷል ሲሉ ተናግረዋል።

በኋላም የናዚ አስተሳሰብ ለዓለም ጦርነት መነሾ ሆኗል። ይህን ዓይነት አስተሳሰቦች በተለያዩ አገራት ላይ ጥፋትን አስከትለዋል ብለዋል።

በመሆኑም የሕወሓት ያለእኔ የተሻለ አገር መምራት የሚችል የለም፣ እኔ ብቻ ሀብት ማጋበስ አለብኝ የሚሉና በጽንፈኝነት ላይ የተመሠረቱ ተያያዥ አስተሳሰቦቹና ርዕዮተ አለሙ የባሰ ጉዳት እንዳያስከትል መሥራት እንደሚገባ አጽንኦት ሰጥተዋል።

ቡድኑ በአሁኑ ወቅትም በሽብርተኝነት የተፈረጀ በመሆኑ በሕግ ታግዷል፤ ነገር ግን አስተሳሰቡ በዜጎች በዕኩልነት መኖር ላይ አደጋ የሚጥል በመሆኑ በትውልዱ ላይ እንዳይሰርጽ የተለያዩ ጥረቶች መደረግ እንዳለባቸው ተናግረዋል።

እኔ የበላይ ነኝ፤ እኔ በኃይል መምራት አለብኝ፤ የሚሉና ሌላውን በመጥፎ ውድድር ላይ በተመሠረተ መንገድ ለመምራት የሚያስቡ እንደሕወሓት ያሉ ቡድኖች አስተሳሰብ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እንዲከስም ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል።

አሸባሪው ሕወሓት የትግራይ ወጣት ላይ ከ48 ዓመት በላይ የሠራበት የሥነልቦና ሥራ ከፍተኛ ነው። በመሆኑም የትግራይ ማህበረሰብ የሽብር ቡድን ላይ ያለውን አመኔታ እንዲያስወግድ ቀረብ ብሎ ሰፊ ጥረት ማድረግ ይገባል።

ከሕግ ዕቀባ ባለፈ አስተሳሰቡን ከማህበረሰቡ ለመነጠል ጥረት ማድረግ ተገቢ ነው። ጽንፍ የወጡ አስተሳሰቦቹን በማስተማርም ሆነ በሕግ አግባብ ማህበረሰቡን ከአሸባሪው ቡድን እሳቤ መነጠል ይጠበቅብናል ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ ሕግ ባለሙያው ከሆነ፤ ከሕወሓት ባለፈ መሰል እኔ ብቻ ነኝ ምርጥ የሚል ጽንፈኛና ለግጭት የሚጋብዝ አስተሳሰብን የሚያራምዱ አካላትም በሕግ ጭምር ታግደው አስተሳሰባቸውም እንዳይስፋፋ በየማህበረሰቡ ላይ መሠራት አለበት፤ ይህ ካልሆነ ዘላቂ ሰላምን ለማግኘት አዳጋች ሊሆን ይችላል።

# «በአንዳንድ ምዕራባውያን ሲደረጉ የቆዩ ጫናዎች ኢትዮጵያ የአፍሪካ የነፃነት አርማ ናት የሚለውን አስተሳሰብ ለማጥፋት ነው»

- አቶ እንዳለ ንጉሴ

የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ፡- አንዳንድ ምዕራባውያን በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት የሚያሳድሩት ተጽዕኖ የአፍሪካን የነፃነት አርማ አሻራ ለማጥፋት ከሚደረግ ሴራ መሆኑን የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር አቶ እንዳለ ንጉሴ ተናገሩ።

የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህር አቶ እንዳለ ንጉሴ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደተናገሩት፤ እነዚህ ምዕራባውያን አገራት በኢትዮጵያ አሸባሪው ሕወሓትን በመደገፍ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ የአፍሪካን የነፃነት አርማ ለማጥፋት ከሚደረግ ሴራ አይተናነስም።

ኢትዮጵያ በአውሮፓ ቅኝ ገዢ ወራሪ ኃይሎች የተሰነዘረባትን ወረራ ሙሉ በሙሉ በራሷ አቅም መክታ ነፃነቷን አስጠብቃ የቆየች ብቸኛ አፍሪካዊት አገር ነች። ኢትዮጵያ በጣሊያን የተቃጣባትን ወረራ በአድዋ ጦርነት በተቀዳጀችው ድል የአውሮፓ ወራሪዎች ሊሸነፉ የሚችሉ መሆናቸውን ለአፍሪካውያን ብቻ ሳይሆን በቅኝ ገዢዎች መዳፍ ስር ወድቀው ለነበሩ ለደቡብ አሜሪካ፣ ካሪቢያንና እሲያ አገራት አሳይታለች።

ኢትዮጵያ በቅኝ ገዢ አውሮፓውያን ስር ወድቀው ለነበሩ የአፍሪካ፣ የደቡብ አሜሪካና ካሪቢያን አካባቢ እንዲሁም የእሲያ አገራት ሕዝቦች ለነፃነታቸው እንዲነሱ በአድዋ ድል መነቃቃት ፈጥራለች ያሉት አቶ እንዳለ፤ ኢትዮጵያ ለሁለተኛ ጊዜ የተቃጣባትን ወረራ በመመከት ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላም ብርቱዎቹን አውሮፓውያን ማሸነፍ እንደሚቻል አረጋግጣ የአፍሪካ የነፃነት ፈርጥ ሆና ቀጥላለች ብለዋል።

እንደ አቶ እንዳለ ገለፃ፤ ኢትዮጵያ የነፃነት ተምሳሌት ከመሆንም አልፋ፣ በቅኝ ግዛት ስር የነበሩት የአፍሪካ አገራት ነፃ ሊወጡ የሚችሉበትና የተባበረች ጠንካራ አፍሪካ ለመመስረት አፍሪካውያንን አነሳስታለች። ይህ ከሌሎች ነፃ የአፍሪካ አገራት ጋር በመሆን የአሁኑን የአፍሪካ ህብረት የወለደውን የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን መመስረት ችላለች።

ኢትዮጵያ በተለያዩ የአፍሪካ አገራት የተቀሰቀሱ ግጭቶች እንዲቀዘቅዙ፣ ውጥረት እንዲረግብ በማድረግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ተጫውታለች። በሩዋንዳ፣ ቡሩንዲ፣ ሱዳን ዳርፉር ለተሰማራው የተባበሩት መንግሥታት ሰላም አስከባሪ ኃይል በኋላም በደቡብ ሱዳንና ሶማሊያ ለተሰማራው የአፍሪካ ህብረት ሰላም አስከባሪ ኃይል ሠራዊት በማዋጣት የአፍሪካን ሰላም ማስጠበቋን የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ አስታውሰዋል።

አንዳንድ ምዕራባውያን በኢትዮጵያ የሚያሳድሩት ተጽዕኖ የአፍሪካን የነፃነት አርማ ለማጥፋት ከሚደረግ ሴራ አይተናነስም ያሉት አቶ እንዳለ፤ የአገርን ሰላም ከመጠበቅ ባለፈ ከደመወዙ በመቀነስ ለአካባቢው ማህበረሰብ ትምህርት ቤት፣ የመጠጥ ውሃ፣ መንገድ፣ ሕፃናትን ሲያስተምርና አዛውንቶችን ሲደግፍ የቆየን ሠራዊት ከኋላ የወጋ አሸባሪ ቡድንን መደገፍ ከአንድ አገር የማይጠበቅ ተግባር ነው ብለዋል።

አንዳንድ ምዕራባውያን ኢትዮጵያ ላይ ከልክ ያለፈ ተጽዕኖ የሚያደርጉት ለሌሎች አገራት የነፃነት ተምሳሌት እንዳትሆን ካለ ውስጣዊ ፍራቻ መሆኑንም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ከምዕራባውያኑ ጋር ስትነፃጸር ረጅም የመንግሥትነት ዕድሜ፣ የዲፕሎማሲ ልምድና የተሻለ ሀሳብ እንዲሁም ነፃነቷንና ሉአላዊነቷን አስከብራ የቆየች አገር ናት። ይህንን ደግሞ አንዳንድ ምዕራባውያን መቀበል አይፈልጉም። ስለዚህ የእጅ አዙር አገዛዝን በአሸባሪው ሕወሓት አማካኝነት ለመተግበር ሲንቀሳቀሱ ይስተዋላል ብለዋል።

እንደ የዲፕሎማሲና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምህሩ ገለጻ፤ እነዚህ ምዕራባውያን በቀጥታ ኢትዮጵያን መውረር እንደማይቻል ስለሚያውቁ አሸባሪውን ሕወሓት ለሚፈልጉት ጉዳይ ተላላኪ በማድረግ ለኢትዮጵያ ውድቀት ከምን ጊዜውም በላይ አትኩረው እየሠሩ ይገኛሉ።

ኢትዮጵያ ደግሞ በነፃነት ምርጫ እያካሄደች፣ የዓባይ ግድብን እየሞላችና የተለያዩ ፕሮጀክቶች እየሠራች ትገኛለች ብለዋል።

ይህ እንቅስቃሴ ለሌሎች አገራት ተምሳሌት እንዳይሆን እንደ ሕወሓት ዓይነት አሸባሪ ቡድን መጠቀም የግድ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ በቁሳቁስ ከመደገፍ ባለፈ በሚዲያዎቻቸው እየደገፉት ይገኛሉ በማለት «እኛ ኢትዮጵያውያን ከምን ጊዜውም በላይ አንድነታችንን አጠናክረን መጓዝ አለብን» ሲሉ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።


ፎቶ፡ በሃዱሽ አብርሃ

# የማይረሳው ክህደት

**ጌትነት ተስፋማርያም**

ጥቅምት ወር አርሶ አደሩ ሰብሉን ለመሰብሰብ ፋታ የሚያጣበት ወቅት ነው። በዚህም የተነሳ አርሶ አደሩ በአንድ በኩል የደረሰው ሰብል በድንገተኛ ዝናብ እንዳይበላሽበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ጊዜው ረዝሞ ሰብሉ እንዳይረግፍ ሲል ጊዜውን በጥድፊያ ያሳልፋል። በዚህ ወቅት አርሶ አደሩን መደገፍ ማለት ከድጋፎች ሁሉ የላቀ ድጋፍ ነው።

ምንጊዜም ከዜጎቹ ጎን የሚቆመው የአገር መከላከያ ሠራዊትም ታዲያ በዚህ ወቅት ከአርሶአደሩ ተለይቶ አያውቅም። በእርሻ ወቅት ያርሳል፤ ሰብል ሲደርስ አብሮ ይሰበስባል፤ ከዚያም አልፎ ካለው ላይ እያካፈለ ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶችን ያከናውናል።

በአካባቢው ከ20 አመታት በላይ የቆየው የሰሜን ዕዝም ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ይህንኑ የተለመደ ተግባሩን ሲወጣ ነው የዋለው፤ በተለይ በወቅቱ የተከሰተውን የአንበጣ መንጋ ሲከላከል።

በአንጻሩ ከዚህ በስተጀርባ ሲጎነጎን የከረመ አንድ ሴራ ስለመኖሩ አልተጠራጠረም። ሴራው ግን ቀጥሏል። ሴራው ደግሞ የአሸባሪው ሕወሓት የሰሜን ዕዝን የማጥቃት ሴራ ነው። ይህ የሴራ ቀነ ቀጠሮም ጥቅምት 24 ሆኖ ተቆርጧል።

ከሌሊቱ አራት ሰዓት ጀምሮም ያልተጠበቀው ነገር ሆነ። በአንድ ጉድጓድ አብረው የታገሉ፤ ተመሳሳይ አገራዊ መለዮ ለብሰው የተዋደቁ ጓዶቻቸው ላይ ክህደትን ፈጸሙ። በአሸባሪው ሕወሓት ሴራ የሰሜን ዕዝ አባላት ከራሳቸው ውስጥ በወጡ የጁንታው አጋሮች ከጀርባቸው ተወጉ። በጓደኞቻቸው ላይ በግፍ ከመተኮሳቸው ባለፈም በኃይል የያዟቸው ጓዶቻቸውን እራቁታቸውን አድርገው ተዘባበቱባቸው።

ሴራው በተለያየ መንገድ ነበር የተፈጸመው፤ ቀን የሠራዊቱ ኃላፊዎችን ለድግስ ጠርተው እዚያው ማፈናቸውን በወቅቱ የመከላከያ አመራር የነበሩት የአሁኑ የኢትዮጵያ በኬንያ አምባሳደር ጄኔራል ባጫ ደበሌ መግለጻቸው የሚታወስ ነው።

ጄኔራል ባጫ የሕወሓት ታጣቂዎች የሠራዊቱ አባላትን ከገደሏቸው በኋላ እሬሳቸው ላይ መጨፈራቸውን ጭምር ሲናገሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን በእንባ ተራጭተዋል።

ከዚያ በኋላ አሸባሪው ሕወሓት በሠራዊቱ ላይ የፈጸመውን ጥቃት መነሻ በማድረግ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በትግራይ ክልል የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ማወጁን ይፋ አደረገ።

የሕወሓት አመራር የነበረው ሴኮቱሬ ጌታቸው መብረቃዊ ጥቃት ፈጽመንባቸዋል፤ መከላከያም አብቅቶለታል ሲል ጥቃቱን አሸባሪው ሕወሓት መፈጸሙን በገዛ አንደበቱ አረጋገጠ።

መብረቃዊ በተባለው ጥቃት ሴት የወታደር አባላት ብልታቸው በብረት ተወግቶ ዘግናኝ ግፍ ተፈጽሞባቸዋል። የሕወሓት ታጣቂዎች አፍነው የያዟቸውን የሠራዊት አባላት አስተኝተው ሲኖትራክ ነድተውባቸዋል። ለማመን የሚከብዱ የግፍ ዓይነቶች በሠራዊቱ ላይ ተፈጽመዋል። ዕለቱ መቼም የሚረሳ አይደለም።

ከጥቃቱ የተረፉ የሠራዊት አባላት ያለምግብና ውሃ ለቀናት በየበረሃው ቢቆዩም የአገር ጉዳይ ነውና እጅ አንሰጥም በማለት በወኔ ተነሱ።

መከላከያ እየሞተም ቢሆን አገር የሚያድን የአላማ ጽናት ያለው ሠራዊት ነውና፤ የሕወሓት ሰዎች እጅ እንዲሰጡ ቢያግባቧቸውም አሻፈረኝ አሉ። ከቀናት በኋላ የአገር መከላከያ ሠራዊትም የተፈጸመበትን ክህደት መክቶ ወደ ፀረማጥቃት ርምጃ መሸጋገሩን አሳወቀ።

በቀራቅር፣ በዳንሻ፣ በሁመራና በተለያዩ አካባቢዎች መከላከያ ከአማራ ልዩ ኃይልና ሚሊሻ ጋር በመቀናጀት ከሃዲውን ማሳደዱን ተያያዘው።

ከጥቅምት 24ቱ ጥቃቱ በኋላ ወደኤርትራ የገቡ የሠራዊቱ አባላትም እንደገና ተደራጅተው በመመለስ የከሃዲውን ቡድን ሴራ እግር በእግር እየተከተሉ መበጣጠሱን ተያያዙት።

በርካታ የትግራይ ሚሊሻዎችና ልዩ ኃይሎች የመከላከያን መልሶ ማጥቃት መቋቋም ባለመቻላቸው እጃቸውን ለሠራዊቱ ሰጡ፤ በርካታ የጁንታው አመራሮችም ተደመሰሱ።

በሌላ በኩል በመላ ኢትዮጵያ የሚገኙ ዜጎች የገንዘብ፣ የዓይነትና የሞራል ድጋፋቸውን ለሠራዊቱ በማቅረብ ደጀንነታቸውን በተግባር ያስመሰከሩበት ጊዜ ነበር። በአጭር ጊዜ እራሱን ያደራጀው መከላከያ ጽናትን አንግቦ በርካታ የትግራይ አካባቢዎችን ከአሸባሪው ሕወሓት ማስለቀቅ የቻለው በቀናት ልዩነት ነበር።

መከላከያ በተቆጣጠራቸው አካባቢዎች የጦር መሣሪያ ማከማቻዎች፣ የመከላከያ ሠራዊት ዩኒፎርሞችና የሃሰት ሰነዶች እንዲሁም አሸባሪው ሕወሓት ለታጣቂዎቹ የሚሰጣቸው አደንዛዥ ዕጾች ጭምር በቁጥጥር ስል ውለው ነበር።

ንስሮቹ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በሕግ ማስከበሩ ዘመቻ ወቅት ስንቅና ትጥቅ ከማመላለስ ባሻገር የተመረጡ ኢላማዎች ላይ ጥቃት በመፈጸም የሠራዊቱን የአሸናፊነት ጉዞ አፋጠኑት። በሰው አልባ በራሪ የታጀበው የአየር ኃይል ጥቃት ለሕወሓት ታጣቂና አመራር ድንጋጤን የፈጠረ ነበር።

የሕግ ማስከበር ዘመቻው 10ኛ ቀኑን ሲያስቆጥር መንግሥት በትግራይ ክልል ሕጋዊ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚያስችለውን ዝግጅት በማድረግ ላይ መሆኑን አሳወቀ።

ሴራው እንዳሰበው ውጤት ያላመጣለት አሸባሪው ሕወሓት ወደአማራ ክልል እና ወደኤርትራ በተከታታይ ሮኬቶችን ተኮሰ። የዚህ ዓላማ ጦርነቱን በማስፋት የምሥራቅ አፍሪካ ለማስመሰል እንደነበረ ለማወቅ ብዙ ምርምር የሚጠይቅ አልነበረም።

ከበርካታ ፀረ ኢትዮጵያ አቋም ካላቸው ድርጅቶችና አገራት ድጋፍ ሲያገኝ የነበረው አሸባሪው ሕወሓት ንጹሃንና የሕዝብ መገልገያ የሆኑ አየር ማረፊያዎች ላይ ጥቃት ቢያደርስም ባለ ረጅም እጅ ሴራው እንዳሰበው አልሰመረለትም።

ይልቁንም መከላከያ ብቃት ያለው ፈጣን የሎጀስቲክ አቅርቦቱን በማጠናከር በድል ላይ ድል መጎናጸፉን ቀጠለ።

ራያ፤ ሽሬ፣ አክሱም፣ አድዋና አዲግራት እንዲሁም ሌሎች ከተሞችም በጥቂት ቀናት በመከላከያ ቁጥጥር ስር ሆኑ። አሸባሪው ሕወሓት ያገታቸውና ሊገድላቸው ቦታ ሲፈልግላቸው የነበሩ አንድ ሺህ መስመራዊ መኮንኖችንና ሕፃናትን ጭምር በከፍተኛ ወታደራዊ ብቃት ከእገታው እንዲለቀቁ ተደረገ።

የሠራዊቱም ሞራል ይበልጥ ከፍ አለ። ከፍተኛ የሕወሓት መሪዎችም በቁጥጥር ስር ከመዋላቸው ባለፈ የተገደሉትንም መንግሥት እያሳወቀ የሕግ ማስከበሩን ቀጥሏል።

ከሦስት ሳምንታት በኋላ ሠራዊቱ መቀሌን ሙሉ ለሙሉ ተቆጣጥሮ የሰሜን ዕዝ ማዘዣንም ዳግም በእጁ ማስገባቱን ሲያሳውቅ ኢትዮጵያውያን ዜናውን በደስታ ነበር የተቀበሉት።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይም በመቀሌ ከተማ ተገኝተው ከመከላከያ ሠራዊት የጦር ጄነራሎች ጋር ውይይት ካደረጉ በኋላ በአጭር ጊዜ ድል ላስመዘገቡ አመራርና አባላቱ ምስጋና በመስጠት ሪፖርታቸውንም ለምክር ቤቱ አቀረቡ።

በትግራይ የተመደበው ጊዜያዊ አስተዳደር ግን ሁኔታዎችን በቁጥጥሩ ስር ሊያውል አልቻለም። ይልቁንም በየቀኑ መከላከያው ላይ ጥቃት የሚፈጽሙ አካላት ተበራከቱ።

በኋላም ለወራት የትግራይ አካባቢዎችን ይዞ የነበረው መከላከያ መንግሥት በወሰነው የተናጠል የተኩስ አቁም ስምምነት መሠረት ከትግራይ ክልል መውጣቱን አስታወቀ።

የአሸባሪው ቡድን ግን የተኩስ አቁሙን ሳይቀበል ታጣቂዎቹን ብቻ ሳይሆን ሕፃናትና አረጋውያንን ጭምር በማሰለፍ በአማራና አፋር ክልሎች ላይ ወረራ ፈጸመ።

ይህን ጥቃቱን በማጠናከር በአማራና አፋር ክልሎች ለሦስት ጊዜ ወረራ በመፈፀም በርካታ ንጹሃንን በአሰቃቂ ሁኔታ ገድሏል፣ ሴቶችን ደፍሯል፤ የሃይማኖት ተቋማትን አቃጥሏል፣ መሠረተ ልማቶችን አውድሟል። ከዚህም ባለፈ ጥፋቱን ለመሸፋፈን በየጊዜው እራሱን ተበዳይ አድርጎ ለማቅረብ ጥረት እያደረገ ይገኛል።

መከላከያ ሠራዊቱ ግን በደምና በአጥንት የከበረችውን ኢትዮጵያን ለመጠበቅ በርካታ ጫናዎችን ተቋቁሞ የተመረጡ የትግራይ ክልል አካባቢዎችን በተለይም የአየር ክልሉን በመቆጣጠር፤ ሰብዓዊ ርዳታ ለሕዝቡ እንዲደርስ እያደረገ ነው።

በጀርባው የተወጋው መከላከያ፤ መቼም የማትረሳዋን ጥቅምት 24 ቀን በህሊናው እያሰበ በጎን ደግሞ ኃላፊነቱን በብቃት የሚወጣ ሠራዊት መሆኑን በተግባር እያሳየ ነው።

የአገር ካስማ በሆነው መከላከያ ሠራዊት ላይ በአሸባሪው ሕወሓት አሳፋሪ ጥቃት የተፈጸመበት ጥቅምት 24 ቀንም እነሆ በተለያዩ ሁነቶች ታስቦ ይውላል። ዕለቱ በሠራዊቱ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያውያንም ዘንድ የማትረሳ ቀን ናት። ለአገራቸው ክብር ሲሉ ለተሰዉ፣ ለተንገላቱና ደማቸውን ላፈሰሱ የመከላከያ ሠራዊት አባላት በልዩ ሁኔታ ክብር ይቸራቸዋል።

ዜና



# የዓለም የትምህርት ትብብር ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሊከፈት ነው

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የዓለም የትምህርት ትብብር ድርጅት ዋና መሥሪያ ቤትን በአዲስ አበባ ለመክፈት የሚያስችል ስምምነት ተፈረመ፡፡

ስምምነቱን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አምባሳደር ተስፋዬ ይልማ እና የዓለም አቀፉ የትምህርት ትብብር ድርጅት ዋና ጸሐፊ መንሱር ቢን ሙሳላም ፈርመውታል፡፡

አምባሳደር ተስፋዬ ይልማ፣ መንግሥት በትምህርት ልማት የሚያደርገውን ጥረት እና ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የሚያደርገውን ትብብር ለማሳደግ የድርጅቱ መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ መከፈት ትብብሩን ያሳድገዋል ብለዋል።

የድርጅቱ ዋና ጸሐፊ መንሱር ቢን ሙሳላም በበኩላቸው፤ በማህበራዊ ፖሊሲዎች፣ ይዘት እና በሥርዓተ ትምህርት ውስጥ አዲስነትን ለመፍጠር ድርጅቱ በኢትዮጵያ ዋና መሥሪያ ቤቱን መክፈቱ ትልቅ አቅም ይፈጥራል ብለዋል።

ስምምነቱ በትምህርት እድገት ተደራሽነት እና ጥራት ላይ ለሚደረገው ጥረትም ከፍተኛ እገዛ እንደሚኖረው መገለጹን ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ ጽህፈት ቤት ያገኘነው መረጃ አመላክቷል፡፡

# ባለሀብቶች በኢትዮጵያ ኢንቨስት እንዲያደርጉ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ጥሪ አቀረቡ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ ምቹ የኢንቨስትመንት ማበረታቻዎች በመኖራቸው ባለሀብቶች ኢንቨስት እንዲያደርጉ ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ ዘውዴ ጥሪ አቀረቡ፡፡ ፕሬዚዳንቷ የአፍሪካ ልማት ባንክ በኮትዲቯር አቢጃን ባዘጋጀው የአፍሪካ ኢንቨስትመንት ፎረም ላይ ተካፍለዋል።

ፕሬዚዳንት ሣህለ ወርቅ ታላላቅ የግልና ተቋማዊ ኢንቨስተሮች በተገኙበት የፕሬዚዳንቶች መድረክ ላይ የተካፈሉ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ስላለው ምቹ የኢንቨስትመንት ዕድልና የትኩረት ዘርፎች ማብራሪያ ሰጥተዋል።

በችግርም ጊዜ መልካም አጋጣሚዎች አሉ፤ ፈተናዎችን እያለፍን የኢንቨስትመንት አማራጮችንም እያሰፋን ነው ብለዋል።

በተለይ አበረታች ውጤት መገኘቱን የጠቆሙት ፕሬዚዳንቷ፤ የግብርና ማቀነባበሪያዎችን ለማስፋት ለኢንቨስተሮች ምቹ አጋጣሚ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ኢትዮጵያ በምታከናውናቸው የልማት ሥራዎች የሕዝቦቿን ኑሮ ለማሻሻል እየተጋች ነው ያሉት ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅ፤ አፍሪካ የምትታይበት መነጽር፣ ድሃ ሕዝቦች የሚኖሩባት ሀብታም አህጉር መሆኗ በቶሎ መለወጥ አለበት ብለዋል።

ፕሬዚዳንቷ «ሴቶች የኢንቨስትመንት ሻምፒዮንስ» በሚል በተዘጋጀው መድረክ ላይም ተገኝተው ንግግር አድርገዋል። በመድረኩም ከተለያዩ አገራት ከመጡ ሴት ባለሀብቶች ጋር ተወያይተዋል።

ፕሬዚዳንት ሣህለወርቅ በቆይታቸው ወቅት ከኮትዲቯር ፕሬዚዳንት አላሳን ዋትራ ጋር ስለ ሁለቱ አገሮች ግንኙነት የተወያዩ ሲሆን፤ አገሪቱ በተመድ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን ለሰጠችው ድጋፍ ማመስገናቸውን ከፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት የተገኘው መረጃ ያመለክታል።

ፕሬዚዳንት ሳህለወርቅና አላሳን ዋትራ የኢትዮጵያና የኮትዲቯር ሁለትዮሽ ግንኙነት በተለይም የኢኮኖሚ ትብብሮች በሚጠናከሩባቸው ጉዳዮች ላይ ምክክር አድርገዋል።

# ሕዝብ ኀዘንና ቁስሉን እንዲያስብ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

መምሪያ የሰሜን ዕዝ የሠራዊት አባላት በማሰብ የህሊና ፀሎት መርሃግብር ተከናውኗል።

አሳዛኙ ክስተት ዕውነተኛ ትምህርት አድርገን ልንወስድ፣ ዛሬ እና ነገአችንን ለማስተካከል የማያዳግም ትምህርት የምንቀምርበት አጋጣሚም አድርገን ልናየው ይገባል ብለዋል።

ሚኒስትሩ እንዳስታወቁት፤ ዕውነተኛ ፈውስ ከጊዜ ጋር በሒደት የሚመጣ መሆኑን በመረዳት፤ በጦርነቱ የተጎዱ የተለያዩ የአገራችን አካባቢዎች የሚገኙ ነዋሪዎችን ስሜትና የልብ ትርታ ማዳመጥ እንዲሁም ተገቢውን የቅርብ ድጋፍ ማድረግ ያስፈልጋል።

ከፊታችን የተደቀነውን እጅግ ውስብስብ እና ጠንካራ የመልሶ ግንባታ ሥራ ፈተናዎችን ከሠላማዊ የሀሳብ ፍልሚያ ጠረጴዛ ላይ ብቻ ለመግዛት ልንጨክን ይገባናል ሲሉ ተናግረዋል።

ከጥቃቱ የፈሪ በትሩ ስንዘራ የተነሳ በአጭር ጊዜ ተደራጅተን በጀግንነት ምላሽ የመስጠታችንን ምክንያት የክህደቱ የጭካኔ ጥግና ቁጭት የፈጠረው ስሜት ነው። አሁንም ያንን የጀግንነት ተግባር በሰላም መንገድ ልንደግመው ይገባል ብለዋል።

ከዚህ ባለፈ ከጥቅምት 24ቱ ጥቃት ትምህርት በመውሰድ ሁሌም የታጠቅንና የተዘጋጀን መሆናችንን እንደሠራዊት ማረጋገጥ ቀዳሚ ተግባራችን መሆኑን በአንክሮ መገንዘብ ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

ዶክተር አብርሃም እንደገለጹት፤ መላው ሕዝብ በሁሉም አካባቢ ሰላም እንዲሰፍን በአዲስ ዕይታ በሙሉ ተስፋና አስተሳሰብ በፍቅርና በይቅርታ የሚጓዝበት መሠረቱ ተጥሏል። በመሆኑም በሰላም ግንባርና መንገድ በመጓዝ የቀደመውን የጀግንነት ተግባር ልንደግመው ያስፈልጋል።

የተፈፀመውን የክህደት ጥቃት የታሪክ መጥፎ ጨለማ አጋጣሚ ብቻ ሳይሆን መከላከያን በአዲስ ለውጥ እያደራጀን ባለበት ወቅት መሆኑ አገር በሒደት ዋጋ ከፍላ የተማረችበት የማይረሳ አጋጣሚያችን ነው ብለዋል።

ከዚህ የጭካኔና የክህደት ጥግ ብዙ ተምረናል፤ ከጥቃቱ ባለፈ የኢትዮጵያን ትንሳኤ በከፍተኛ ስጋትነት የሚቆጥሩ ኃይሎች በዙሪያችን መሆናቸውን አይተናል ሲሉ ገልጸዋል።

በመሆኑም አቅማችንን የማጎልበቱ የማጠናከር ጉዳይ የሚቆም አይደለም ያሉት ሚኒስትሩ፤ መላው ሕዝብ በተለይም ወጣቱ ሰላምና አንድነታችንን ለማስጠበቅ በነቂስ ወጥቶ እንደተሰለፈ ሁሉ አሁንም ሠራዊቱን ለማጠናከር የሚደረገውን ጥረት እንዲደግፍ ጥሪ አቅርበዋል።

እንደ ሚኒስትሩ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ሠላሟና የግዛት አንድነቷን ለማስጠበቅ በአራቱም ማዕዘናት የተሠማራው ሠራዊታችን የዘላቂ ሠላማችን ፍቱን መድኃኒት መሆኑ ይታወቃል።

በህብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያ ልክ የተገነባ ዘመናዊ የመከላከያ ኃይል የመገንባት ጅምራችንን አጠናክረን እንቃጥላለን ሲሉ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

# ጀግኖች ኢትዮጵያውያን በመሬት ላይ...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

በማንሳት በደቡብ አፍሪካ በነበረው የሰላም ድርድር ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች በመሬት ላይ ያስገኙትን ታሪካዊ ድል ዳግም የሚያስረግጥ የሰላም ድል ማግኘት ተችሏል ብለዋል።

በደቡብ አፍሪካ በተካሄደው ድርድር የተገኙ ድሎችን የዘረዘሩት ጠቅላይ ሚኒስትሩ በድርድሩ ከተገኙ ዋና ዋና ድሎች መካከል አንደኛው የኢትዮጵያ ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት ለድርድር አይቀርብም የሚለው መሆኑንና ይህ ሃሳብ በሁለቱም ወገን ተቀባይነት ማግኘቱን ተናግረዋል። በዚህም ለኢትዮጵያ አንድነት የሞቱና የቆሰሉ ጀግኖች ራዕያቸውና ህልማቸው ዕውን ሆኗል ሲሉ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል በአንድ አገር መኖር ስለሚገባው የአገር መከላከያ ሠራዊት አስፈላጊነት ላይ መግባባት ላይ እንደተደረሰ ጠቅሰዋል። እንደ ጋሞ ባሉ አባቶች እግር ሥር ያደገ ሁሉ ነገር በንግግርና በውይይት እንደሚፈታ ያውቃል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በአንድ አገር ውስጥ ከአንድ መከላከያ በላይ አያስፈልግም በሚለው ጉዳይ ከስምምነት ላይ ተደርሷል ሲሉ አብራርተዋል።

ሕጋዊነትን ማስፈን ላይ በተደረገው ውይይትም ሕግ መከበር ይኖርበታል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ ይህ ካልሆነ ተቋማዊነት እና አገራዊ ቁመና እንደሚሸረሸር በመጠቆም ሕገወጥ በሆነ መንገድ የተደረገው ምርጫ በሕጋዊ ምርጫ መተካት አለበት የሚለው በሁለቱም ወገኖች ተቀባይነት ማግኘቱን ገልጸዋል።

ከዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የይገባኛል ጥያቄ የሚነሳባቸው እና አከራካሪ የሆኑ ቦታዎችን ዳግም የሰው ልጅን ሕይወት ሳይጠይቁ በሰላም፣ በውይይት እና በአገሪቱ ሕግ መሠረት ብቻ ምላሽ እንዲያገኙ በሁለቱም ወገኖች ከስምምነት ተደርሷል ሲሉ አብራርተዋል።

በአጠቃላይ ደቡብ አፍሪካ ላይ በነበረው ድርድር ኢትዮጵያ ያቀረበችው ሃሳብ 100 በመቶ ተቀባይነት ማግኘቱን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ገልጸዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ባስተላለፉት መልዕክት ጀግንነት ማለት ማሸነፍ ብቻ አለመሆኑን ገልጸው፤ ጀግንነት ማለት ከድል በኋላ ደግነት ማለት በመሆኑ ከድል በኋላ ይቅር ማለት ተገቢ እንደሆነ ጠቁመዋል።

ኢትዮጵያውያን ጀግኖች ብቻ ሳንሆን ፈጣሪን የምንፈራና የምናከብር ሰዎች ስለሆንን ያገኘነውን የሰላም ዕድል በታላቅ ክብር ተቀብለን እና በሙሉ ልብ ይቅር ብለን የኢትዮጵያን አንድነትና ሰላም ለመመለስ እንዲሁም የልመናን ጣጣ ለማፍረስ እንፈልጋለን ብለዋል።

ኢትዮጵያውያን የተገኘው የሰላም ዕድል ለኢትዮጵያ ታላቅ ድል እና እጃቸውን ያስገቡ የኢትዮጵያ ጠላቶች ያፈሩበት ስለሆነ በሙሉ ልብ ትግራይን ለመገንባት እና ወደ ቀደመው የአገሩ ስሜት ለመመለስ በሕብረት እንድንቆም በታላቅ ትህትና እጠይቃችኋለሁ ሲሉም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ጉባዔው የሕዝብ ለሕዝብ ትስስርን...

ከ1ኛው ገፅ የዞረ

ያገረሸው ጦርነት እንዲቆም ጥሪ የሚያደርግ መግለጫ ማውታጣታችን የሚታወስ ነው ብለዋል። በመጨረሻም የፈጣሪ ፍቃድ ሆኖ የሰላም ዜና በመሰማቱ ለፈጣሪ ምስጋና አንደሚያቀርቡ ገልጸዋል።

የሰላም ስምምነቱ ይዘት ጦርነትና ውጊያ ከማቆም ባለፈ በአገሪቱ ዘላቂና አስተማማኝ ሰላም ለማምጣት የሚረዳ እንደሆነ ተገንዝበናል ያሉት ቀሲስ ታጋይ፤ በተለይም ጦርነት የወጣቱን ሕይወት የሚቀጥፍ፣ ሕፃናትን ያለአባት፣ አረጋውያንን ያለጧሪ የሚያስቀር ክፉ ተግባር ከመሆኑም በላይ የአገራትን ሀብት የሚያወድም ነው ሲሉ አብራርተዋል። በመሆኑም የሰላም ስምምነቱ በእጅጉ አስፈላጊና ወቅታዊ ውሳኔ በመሆኑ ጉባዔው ውሳኔውን በሙሉ ልብ የሚደግፈው መሆኑን ገልጸው፤ የሰላም ስምምነቱ በተሟላ ሁኔታና ያለምንም እንከን እንዲተገበር ማሳሰቢያዎችንና ምክረ ሃሳቦችን አቅርበዋል።

ሁለቱም ወገኖች ችግሮችን በሰላም ለመፍታት ጦርነትንና ውጊያን በማቆም ሁሉን አቀፍና ዘላቂ ሰላም ለማምጣት የሚያስችል ስምምነት ላይ በፊርማቸው ማረጋገጣቸው በእጅጉ የሚያስመሰግን ተግባር መሆኑን ገልጸው፤ በተለይም የተደረሰበት የሰላም ስምምነት ሁሉንም ወገን አሸናፊ የሚያደርግ መሆኑ አንስተዋል።

በተጨማሪም ስምምነቱ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚያስከብር በመሆኑ ለስምምነቱ ተፈፃሚነት ሁሉም ወገን ቁርጠኛ በመሆን እንዲሠሩ በአጽንኦት የጠየቁት ዋና ጸሐፊው፤ በተለይም በቀጣይ የሕዝብ ለሕዝብ ግንኙነቱን ለማጠናከር ተገቢው ሁሉ እንዲከናወን እናሳስባለን ብለዋል።

ቀሲስ ታጋይ፤ በየሰላም ስምምነት አሸናፊና ተሸናፊ የለም፤ አሸናፊው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ነው ያሉ ሲሆን ይህንን ውሳኔ በአሉታዊ መልኩ የሚቀሰቅሱና የሚያቀነቅኑ አካላት ከድርጊታቸው እንዲቆጠቡ በአባትነት በአጽንኦት እናሳስባለን ብለዋል።

በጦርነቱ የተጎዱ ወገኖችን ለማቋቋምና የሰብአዊ ድጋፍ ለማድረግ ሁሉም ኢትዮጵያዊ፣ ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ ልዩ ትኩረት ሰጥተው እንዲሠሩ በአጽንኦት በፈጣሪ ሥም እናሳስባለን ያሉት ቀሲስ ታጋይ፤ የሰላም ስምምነቱ ዘላቂነት እንዲኖረውና መልካም ፍሬ እንዲያፈራ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደየ እምነት ሥርዓቱ ወደ ፈጣሪ ልመና እንዲያቀርብ አደራ ብለዋል።

በመጨረሻም የሰላም ስምምነቱ እውን እንዲሆን አስተዋጽኦ ላደረጉ ሁሉ በተለይም ለአፍሪካ ኅብረት ኮሚሽን መሪዎች፣ የሰላም ውይይቱን ላስተባበሩት የአፍሪካ ተወካዮች እና ለደቡብ አፍሪካ መንግሥት ልባዊ ምሥጋናቸውን አቅርበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አሸናፊዋ ኢትዮጵያ አሁንም አሸንፋለች!

ኢትዮጵያ የአሸናፊነት ተምሳሌት ናት። ለዚህ ደግሞ በየዘመኑ በተለያዩ መስኮች የተጎናጸፈቻቸው ድሎች ማሳያዎች ናቸው። በጦርነት፣ በዲፕሎማሲ፣ አሁን አሁን ደግሞ በልማቱ መስክ እንዲሁም ዘላቂ ሰላምን በማምጣት አሸናፊነትን በመጎናጸፍ ትታወቃለች።

ይህች የአሸናፊነት ተምሳሌት አገር እነሆ ዛሬም ሌላ አሸናፊነትን ተጎናጽፋለች። በሰሜን ኢትዮጵያ ላለፉት ሁለት ዓመታት ሲካሄድ የቆየውን ጦርነት በሰላም ለመቋጨት በአፍሪካ ህብረት አማካይነት በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማ ለአስር ቀናት በኢትዮጵያ መንግሥትና በአሸባሪው ሕወሓት መካከል በተካሄደው የሰላም ንግግር መጨረሻ ጦርነቱን በሰላማዊ መንገድ ለመቋጨት በተደረሰው ስምምነት አሸናፊነትን ተጎናጽፋለች።

ስምምነቱ የኢትዮጵያን ጥቅም ያስከበረ ሆኖ ተገኝቷልና ይህም የአገሪቱ አሸናፊነት ሌላው ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል። ይህ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱንና የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም ያስከበረ ስምምነት፣ የአገሪቱን የአሸናፊነት ተምሳሌትነትም አድሶታል። በዚህም ኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያ ወዳጆች ሁሉ በእጅጉ ሊኮሩ ይገባል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በአርባ ምንጭ ከተማ ለተሰበሰበ ሕዝብ ባደረጉት ንግግር ‹‹በሰላም ንግግሩ ኢትዮጵያ ያቀረበችው ሀሳብ መቶ በመቶ ተቀባይነት አግኝቷል›› ሲሉ ገልጸዋል። ስምምነቱ መንግሥት ካስቀመጠው አቅጣጫ ጋር የተጣጣመ፣ አሸባሪው ሕወሓት ትጥቅ እንዲፈታ የሚያደርግ፣ የመላ ኢትዮጵያ ሕዝብን ፍላጎት የሚያሟላ፣ ዘላቂ ሰላምን የሚያረጋግጥ እና የትግራይን ሕዝብ መሠረታዊ ችግሮች የሚፈታ ሲል የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት አስታውቋል።

ሁለት ዓመት የዘለቀውን ጦርነት የሚያስቆም፣ በኢትዮጵያ ሊኖር የሚገባው አንድ የመከላከያ ሠራዊት ብቻ መሆኑን የሚያጸና በሚልም መንግሥት ገልጾታል። በዚህ የሰላም ስምምነት ያሸነፈችው ኢትዮጵያ መሆኗንም ነው መንግሥት ያስገነዘበው።

በእርግጥም በስምምነቱ ኢትዮጵያ አሸንፋለች። ታላቅ ድልም ነው የተመዘገበው። ኢትዮጵያ ከመጀመሪያም የዘላቂ ሰላምን ሀሳብ በማቀንቀን ስትጓዝ እንደመቆየቷ፣ መንግሥት ጦርነት ከመጀመሩ በፊትም ሆነ እየተካሄደ እያለ ስለዘላቂ ሰላም ሲያስገነዝብና ሲሠራ እንደመቆየቱ፣ ድሉ ድንገት ከተፍ ያለ ድል አይደለም። አሸናፊነቱ ለኢትዮጵያ የሚገባት ነው።

መንግሥት በጦርነቶች በተገኙ ድሎች ሳይኩራራ የሰሜን ኢትዮጵያ ችግር ሊፈታ የሚችለው በሰላማዊ አማራጭና በንግግር ነው ብሎ አጥብቆ አስገንዝቧል፤ ለዚህም ቁርጠኝነቱን በተግባር አሳይቷል። አሸባሪው ሕወሓት በሰሜን እዝ ላይ ክህደት ከመፈጸሙ ከዛሬ ሁለት ዓመት በፊትም በወቅቱ አንዣቦ የነበረው የጦርነት ደመና እንዲገፈፍ በአገር ሽማግሌዎች፣ በሃይማኖት አባቶች፣ በእናቶች፣ በአምባሳደሮች በኩል ትግራይ ድረስ በመሄድ ስለአገሪቱ ሰላም ተሠርቷል፤ መንግሥት በሕግ ማስከበር ዘመቻ ድል በእጁ እያለም ለዘላቂ ሰላም ሲል የተናጠል ተኩስ አቁም በማድረግ ሠራዊቱን ከትግራይ አስወጥቷል፤ በሕግ ማስከበር ወቅት ተይዘው በሕግ ጥላ ስር የነበሩ የሕወሓት አመራሮችን ክስ በማቋረጥ ከእስር ፈትቷል።

ዓለም አቀፍ ማህበረሰቡም ይሁን የአፍሪካ ህብረት ለሰላም ሲያቀርቡ ለነበረው ጥሪ ሁሉ በጎ ምላሽ በመስጠት አብሮ ሠርቷል፤ በተለይ ለአፍሪካውያን ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ የሚል አቋም በመያዝ የአፍሪካ ኅብረት ለዘላቂ ሰላም እንዲሠራ ጥረት አድርጓል፤ የዲፕሎማሲ ሥራዎችንም ሠርቷል። አገራዊ የምክክር መድረክ በማቋቋም ኢትዮጵያውያን በአገራቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሚመክሩበትን መድረክ ፈጥሯል።

በደቡብ አፍሪካው የሰላም ንግግር ኢትዮጵያ የተጎናጸፈችው ታላቅ ድልም ለዘላቂ ሰላም አጥብቃ በመሥራቷ ያገኘችው አሸናፊነት ነው። ይህ አሸናፊነት እንዲመዘገብ መላው የጸጥታ እና የደህንነት ኃይሎች እንዲሁም መንግሥትና ሕዝብ ብዙ ዋጋ ከፍለዋል፤ በዲፕሎማሲው መስክም ብዙ ተሠርቷል። በዚያው ልክም ኢትዮጵያ የሚገባትን የአሸናፊነት ክብር ተጎናጽፋለች።

ይህ የኢትዮጵያን ፍላጎቶች ያሟላ፣ ሉአላዊ አገርነቷን በእጅጉ ያጸና ስምምነት በኢትዮጵያውያን መካከል የጥፋት እጃቸውን እያስገቡ ሰላማቸው እንዲደፈርስ፣ ልማት እንዲስተጓጎልና በዓለም ሕዝብ ዘንድ የሚታወቀው የአገሪቱ ገጽታ እንዲበላሽ ሲያደርጉ የቆዩ አንዳንድ የውጭ ኃይሎችና የሚዘውሯቸውን ዓለም አቀፍ ተቋማትና መገናኛ ብዙኃን ያሳፈረም ነው። በአንጻሩ ለአፍሪካውያን ችግር አፍሪካዊ መፍትሄ በሚል የሚሠሩትን ኢትዮጵያን ጨምሮ እንደ ኬንያ እና ደቡብ አፍሪካ ያሉትን የአፍሪካ አገሮች ያኮራም ሆኗል። ታላቅ የዲፕሎማሲ ድል የተመዘገበበት ተብሎም ሊወሰድ ይችላል።

ስምምነቱ ኢትዮጵያውያን ዋጋ የሚከፍሉበትን ጦርነት የሚያስቆምና ታላቅ ክብር ሊሰጠው የሚገባ ነው። ባለፉት ሁለት ዓመታት በተካሄዱ ጦርነቶች አያሌ ኢትዮጵያውያን ተሰውተዋል። ስለሆነም ስምምነቱ ሌሎች ተጨማሪ መስዋዕትነትን ያስቀራል። የአገር እና የዜጎች ሀብትን ከውድመት የሚጠብቅም ይሆናል። ለቀጣይ ልማትም ዋና መደላድል በመሆን ያገለግላል።

የኢትዮጵያ ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት በስምምነቱ መሠረት ለድርድር የማይቀርብ ጉዳይ ነው። ስለሆነም አስፈላጊው ነገር ለዚህ ስምምነት ተግባራዊነት መሥራት ነው ።

ቀጣዩ ሥራ ስምምነቱን መጠበቅና ለተግባራዊነቱ አጥብቆ መሥራት ይሆናል። በዚህ ስምምነት ላይ ተቆሞ ነው ቀጣዩ የሰላም ሥራ የሚከናወነው። ኢትዮጵያ ለሰላም ባላት ጽኑ እምነት፣ እስከ አሁንም ለሰላም ብዙ ዋጋ የከፈለች እንደመሆኗ በዚህ በኩል አጥብቃ እንደምትሠራ ይታወቃል። በአጠቃላይ በሰላም ንግግሩ አሸናፊዋ ኢትዮጵያ አሁንም አሸንፋለች፤ ይህን አሸናፊነቷንም ስምምነቱን በመተግበር ትደግመዋለች!


ኢፕድ

አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ዋና አዘጋጅ

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

አድራሻ

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ

ስልክ - 011-1-26-43-39

ማከፋፈያ

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


## ‹‹ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ብላችሁ ብዙ የተጋችሁ የቅርብና የሩቅ አገራት ኢትዮጵያ የማትፈርስ፣ የፀናች፣ የምትበለፅግ የአፍሪካ ፈርጥና ኩራት ናት››

*ዶክተር ዐቢይ አሕመድ*

*የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር*

**አስምረት ብስራት**



የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በኢፌዴሪ መንግሥትና በአሸባሪው ትህነግ መካከል በደቡብ አፍሪካ ለቀናት ያህል የተደረገውን የሰላም ንግግር መቋጫ አስመልክተው በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል በምትገኘው አርባ ምንጭ ከተማ በአካባቢው ስላለው የልማት እንቅስቃሴን እየጎበኙ ባሉበት ወቅት የሰላም ንግግር እና ስምምነቱን አስመልክተው ያስተላለፉትን መልዕክት እንደሚከተለው አቅርበነዋል፡፡

ክቡር ኃይለማርያም ደሳለኝ የኢፌዴሪ የቀደሞው ጠቅላይ ሚኒስትርና የአርባ ምንጭ ልዩ አምባሳደር፤ ክቡር አቶ ደመቀ መኮንን የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር፤ ክቡር አቶ አደም ፋራህ የብልፅግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት፤ ክቡር አቶ ታገሰ ጫፎ የጋሞ ሽበላ፤ የተከበራችሁ የሁሉም ክልል ፕሬዚዳንቶች፤ ሚኒስትሮች ፤ ከንቲባዎች፤ እዚህ ስፍራ የተገኛችሁ እንግዶች በሙሉ፤ አካል ብቻ ሳይሆን አይን ማጥገብ ብቻ ሳይሆን፤ ለመንፈስ እረፍት ወደምትሰጠው ውቧ ገነቷ አርባ ምንጭ እንኳን በሰላም መጣችሁ።

ብዙ ቦታ ለአካል እረፍት ይሰጣል፤ አርባ ምንጭ ጨንቻ ግን ለመንፈስም እረፍት ይሰጣል። እነ ኃይሌ የአርባ ምንጭ ሙዝ፣ የአርባ ምንጭ አፕል፣ የአርባ ምንጭ ወተት፣ የአርባ ምንጭ የእጅ ጥበብ የሆነው ሸማ ብለው ለዘመናት ሲናገሩ ነበር፤ ዛሬ ልነግራቸው የምፈለገው ግን የአርባ ምንጭ ጣዕም ያለው የሰላም መንፈስም ይጨመርበት። ትናንት ወደ ጨንቻ ሄደን ነበር፤ በጨንቻ ወተትና አፕል በየጓሮው የሚታይበት፤ ደጋግ አርሶ አደሮች ያሉበት ኢትዮጵያዊነት ኩራት የመሆን ተምሳሌት የሆነበትን ስፍራ ለማየት ዕድል አግኝቻለሁ።

ጨንቻ፣ አርባ ምንጭ፣ ሳውላ፣ ሶዶ፣ ዳውሮ፣ ጂንካ፣ ጂማ፣ ኢትዮጵያ በጋራ የምንቆምባትን ምድር የሰጠን ፈጣሪ የተመሰገነ ይሁን። ከጥቂት አመታት በፊት በምዕራብ ኢትዮጵያ የንግድ፣ የፈጠራ የኢትዮጵያዊነት ምሳሌ ወደ ሆነችው ወልቂጤ ከተማ የመሄድና የመጎብኘት ዕድል ነበረኝ።

የወልቂጤ ሕዝብ ዛሬ በአርባ ምንጭ እንደምናየው በከፍተኛ ደስታ እና የሰላም መንፈስ ተቀብሎን እዛው እያለን የኢትዮጵያና የኤርትራ የሰላም ዜና ለመጀመሪያ ጊዜ በወልቂጤ ከተማ ነበር የሰማነው። እንደ ጉራጌ ሕዝብ ሰላም ወዳድ፣ ሥራ ወዳድ፣ አርቆ አሳቢና በኢትዮጵያዊነቱ ፅኑ አቋም ያለው የአርባ ምንጭ ሕዝብ ከልቡ ደግነትና ቸርነት የተነሳ እዚህ እያለን የኢትዮጵያ የሰሜን ጦርነት የሚያበቃበት ሰላም ትናንት ተነገረ።

እኛ ሰላም የምንወድ ሕዝቦች፤ እኛ ሰላምን የምንሻ ሕዝቦች፤ እጅግ በምንወዳት ገነት በሆነችው የፍቅር ከተማ ውስጥ የሰማነው ዜና ሁልጊዜ የማይረሳ በመሆኑ ጋሞዎች እንኳን ደስ አላችሁ።

ዛሬ እዚህ የተገኘነው ለሁለት መሠረታዊ አላማ ቢሆንም፤ ሦስተኛ ጉዳይ ተጨምሯል። አንደኛው የጋሞ፣ የጎፋ፣ የወላይታ፣ የጉራጌ፣ የስልጤ፣ የሀዲያ፣ የከምባታ የዚህ አካባቢ ሕዝቦች በሙሉ ኢትዮጵያ ስትደፈር፤ የኢትዮጵያ ልጆች በግፍ ሲገደሉ፤ ‹ይህንን ለመስማት ለማየት ዝግጁ አይደለንም› ብላችሁ በፈቃድ

‹‹ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

# ‹‹ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ብላችሁ ብዙ የተጋችሁ...

ከገጽ 5 የዞረ

> **አንተ የተከበርክ፣ ለሕይወትህ የማትሳሳ፣ ሁለት ዓመት ሙሉ በብርድ፣ በዝናብ፣ በየጫካው የተኛህ፣ አንተ የኢትዮጵያ ኩራት፣ የአገር መከላከያ፣ አንተ የኢትዮጵያ ወኔ፣ አንተ የኢትዮጵያዊነት ምልክት፣ አንተ የጀግንነት ምልክት፣ በአንተ ድካም፣ በአንተ መቁሰል፣ በአንተ ሕይወት ኢትዮጵያ ዳግም ቆማ በክብር መናገር ስለቻለች መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአገር መከላከያ ያለንን ታላቅ አክብሮትና ፍቅር ካለንበት በመቆም እንድናሰማ በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ**

በደስታ በልጆቻችሁ ደምና ሕይወት የኢትዮጵያን ሉአላዊነት ለማፅናት ትልቅ ዋጋ ስለከፈላችሁ ሁሉም አመራሮች ‹እናመሰግናችኋለን› ለማለት ነው ። ሁለተኛው ፕሮግራማችን ከዚህ ፕሮግራም በኋላ የሚጀመር ስለሆነ እሱን እዚህ አልገልፀውም። ሦስተኛው ግን ትናንት የሰማችሁት፤ የሰማነው የሰላም ድርድር ጉዳይ ቀደም ብዬ ካነሳሁት አላማዎች የሚያንስ ስላልሆነ በተወሰነ ደረጃ ነካ አድርጌ ለማለፍ እወዳለሁ።

እንደምታስታወሱት፤ የዛሬ ሁለት አመት ባልተገባ መንገድ ከወንድሞቻችን እጅግ አሳዛኝ ጥቃት ተሰንዝሮብን ነበር። የኢትዮጵያ ወንድና ሴት ልጆች በገዛ ወንደሞቻቸው ባልተገባ ሁኔታ በተኙበት ታርደው፣ ተገድለው፣ ተገፍተው ነበር።

ያ ሁኔታ ሁላችንንም ያስቆጣ በኢትዮጵያ ሉአላዊነትና አንድነት አንደራደርም፤ ቢሮ ተቀምጠን መምራት ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ክብር ከተመጣ የጥይት አረር በግንባራችን ለመቀበልና ሉአላዊነታችንን ለማስከበር ዝግጁ መሆናችንን ለመላው የኢትየጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ለዓለም ሕዝብ ያሳየንበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር።

ነገር ግን፣ እንኳን እርስ በርስ በወንድማማቾች መካከል ቀርቶ በማንኛውም አገር መካከል ቢሆን የሚወደድ፣ የሚናፈቅ፣ የሚፈለግ ነገር አይደለም፡፡ ጦርነት የሰው ሕይወት ይቀጥፋል፤ እጅ እግር ያሳጥራል፤ ንብረት ያወድማል፤ ጥላቻን ያበዛል፡፡ ከዚህ የተነሳ ለፈጣሪ ምስጋና መስጠት የሚገባው ሕዝብ የእርግማን ምንጭ ይሆናል፡፡ ጦርነትን እኛ አብዝተን እንጠላለን፡፡ እኛ የምንፈልገው ሰላምና ብልጽግና ነው፡፡

በደቡብ አፍሪካ በነበረው የሰላም ድርድር ጀግኖች የጋሞ ልጆች፣ ጀግኖች የኢትዮጵያ ልጆች በመሬት ላይ ያስገኙትን ታሪካዊ ድል ዳግም የሚያስረግጥ የሰላም ድል ማግኘት ተችሏል። ከተገኙ ዋና ዋና ድሎች መካከል አንደኛ፣ የኢትዮጵያ ሉአላዊነትና የግዛት አንድነት ለድርድር አይቀርብም የሚለው በሁለቱም ወገን ተቀባይነትን አግኝቷል። ለኢትዮጵያ አንድነት የሞቱ የቆሰሉ፣ ባልተገባ ሁኔታ የወደቁ ጀግኖች እንኳን ደስ ያላቸው፤ ሕልማቸው እውን ሆኗል፡፡

ሁለተኛ፣ በሰለጠነው ዓለም እንደ ጋሞ ባሉ ሽማግሌዎች ስር ያደግ ሕዝብና አገር ነገር በምክክርና በንግግር እንደሚጨረስ ስለሚያወቅ በአንድ አገር ውስጥ ከአንድ መከላከያ በላይ አያስፈልግም የሚለው ጉዳይም ከስምምነት ተደርሷል።

ሦስተኛ ሕጋዊ እና ሕጋዊነትን ማስፈን ለአንድ አገር ህልውና መሠረት ስለሆነ የራሳችንን ሕግ የማናከብር ማሻሻል ሲኖርብንም በሕግ አግባብ የማናደርግ ከሆነ ተቋማዊነት አገር የሚለው ቁመና ስለሚሸረሽር ሕገወጥ በሆነ መንገድ የተደረገው ምርጫ በሕጋዊ ምርጫ መተካት አለበት የሚለውም በሁለቱም ወገኖች ተቀባይነት አግኝቷል። ከዚህ በተጨማሪ በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የይገባኛል ጥያቄ የሚነሳባቸውና አከራካሪ የሆኑ ቦታዎች ዳግም የሰው ልጅን ሕይወት ሳይጠይቁ በሰላም፣ በድርድርና በአገሪቱ ሕግ መሠረት ብቻ ምላሽ እንዲያገኙ በሁለቱም ወገኖች ከስምምነት ተደርሷል።

ደቡብ አፍሪካ ላይ በነበረው ድርድር ኢትዮጵያ መቶ በመቶ ያቀረበችው ሀሳብ ተቀባይነት አግኝቷል። ታዲያ የጋሞ ጀግኖች ጀግንነት ማለት ማሸነፍ ብቻ አይደለም። ጀግንነት ማለት ከድል በኋላ ደግነት ማለት ነው። ከድል በኋላ ይቅር ማለት ነው። እኛ ጀግኖች ብቻ ሳንሆን ፈጣሪን የምንፈራ የምናከበር ሰዎች ስለሆንን ያገኘነውን የሰላም ዕድል በታላቅ ክብር የምንቀበል እና በሙሉ ልብ ይቅር ብለን የኢትዮጵያን አንድነት እና ሰላም በመመለስ የልመናን ጣጣ ለማፍረስ ስለምንፈልግ እጅግ የምወዳችሁ የጋሞ ሕዝቦች እንዲሁም በመላው ኢትዮጵያ የምትገኙ ዜጎች የተገኘው የሰላም እድል ለኢትዮጵያ ታላቅ እድል ስለሆነ ብዙ እጃቸውን ያስገቡ ጠላቶቻችሁ ያፈሩበት ስለሆነ፤ በሙሉ ልብ ትግራይን፣ የትግራይ ሕዝብን ለመገንባትና ወደ ቀደመው ወደ አገሩ ስሜት ለመመለስ አብረን እንድንቆም በታላቅ ትህትና እጠይቃችኋለሁ።

የአማራ ጀግና፣ የአፋር ጀግና፣ የኦሮሞ ጀግና፣ የሱማሌ ጀግና፣ የደቡብ ምዕራብ ጀግና፣ የደቡብ ጀግና ጀግንነታችን የሚረጋገጠው ካለን አካፍለን በትግራይ የተጎዱ ወገኖቻችንን ማጉረስ ስንችል ነው። ካለን አካፍለን በማጉረስ ፍቅር በመስጠት ኢትዮጵያዊነት የሚሻል፣ ኢትዮጵያዊነት የላቀ፣ ኢትዮጵያዊነት ምስጢርና ጥበብ መሆኑን እርስ በእርሳችን ብቻ ሳይሆን ለዓለም ተጨማሪ ትምህርት መስጠት ስለሚኖርብን እናንተ ያሸነፋችሁ ጀግኖች ልባችሁን ከፍታችሁ ወደኋላ ሳተመለከቱ ኢትዮጵያን ለመገንባትና አንድነቷን ለመጠበቅ ያላችሁን በመስጠት በጉልበት በማገዝ፣ ፍቅር በማጋራት፣ ክፉ ከመናገር በመቆጠብ፣ ደጋግ ጀግና የኢትዮጵያ ልጆች እንድትሆኑ በታላቅ ትህትና ደግሜ ልጠይቃችሁ እፈልጋለሁ።

ለአገር አንድነት ሕይወት ከከፈልን፣ ለአገር አንድነት ደማችንን ካፈሰስን፣ አጥንታችንን ከከሰከስን፣ ለሰላምና ለአንድነት ላባችንን ብናፈስ፣ ከኪሳችን ብናወጣ ፀጋ በረከት እንጂ ጉድለት ስለማይሆን ኢትዮጵያውያን ልባችሁ ይስፋ፤ ወደኋላ አትመልከቱ። ሰላማችን ወደኋላ እንዳይመለስ በፀሎታችሁ፣ በሀሳባችሁ፣ በድርጊታችሁ ከእኛ ጋር በመቆም ዘላቂ ሰላም እንዲረጋገጠና ኢትዮጵያ እፎይ እንደትል የበኩላችሁን ሚና እንድትጫወቱ አደራ ልላችሁ እፈልጋለሁ።

ለትግራይ ሕዝብ በተደጋጋሚ ትግራይ አገራችን ሕዝቡም ሕዝባችን ነው ስንል መቆየታችን ይታወቃል። ብዙ ያልተገባ መቆሳሰል፣ ያልተገባ መደማማት፣ ያልተገባ ጉዳት በእያንዳንዳችን ደርሷል፡፡ ከሁሉ በላይ በኢትዮጵያ ደርሷል። የመጨረሻው መልዕክቴ፣ ለትግራይ ሕዝብ ነበር፤ የትግራይ ሕዝብ በተደጋጋሚ ሕዝባችን ምድሩም ምድራችን እንደሆነ ስንገልፅ ቆይተናል፡፡

ተጠቃ ብለን ስናስብ በትግራይ ምድር የልጅነት ወራታችንን ያጠፋንና ትግራይን የተከላከልን መሆናችንን ታሪክ ይመሰክራል። ዛሬም ያ ልባችን በቦታው ላይ ነው ያለው፡፡ ለመላው የትግራይ ሕዝብ ማስተላለፍ የምፈልገው መልዕክት አላስፈላጊ ጦርነት፣ አላስፈላጊ ጉዳት፣ አላስፈላጊ ኢትዮጵያን አጋልጦ የመስጠት ሂደት በዚህ ይብቃ።

ብዙ መከፈል የማይገባው ዋጋ ተከፍሏል፤ ብዙ ደም ፈስሷል፤ ንብረት ወድሟል፤ ኢትዮጵያን የዓለም ሚዲያዎች የሚያውቁም የማያውቁም ትልቁም ትንሹም በከፍተኛ ደረጃ አንጓጠዋታል፤ አሳንሰዋታል፤ ይብቃ። ብዙ ጊዜ ከሰላም ድርድር በኋላ ሽፍጦች፣ ተንኮሎች፣ ደባዎች ይታያሉ። የተከበርከው የትግራይ ሕዝብ እኛ ልባችንን ከፍተን ሰላም ለማምጣት ዝግጁ ስለሆንን ይህንን የገባነውን ቃል ለመጠበቅ ከሌሎች ወንድም ሕዝቦች ጋር በጋራ በመሆን የበኩልህን ሚና እንድትወጣ ተንኮል፣ ክፋት፣ ሽር እዚህ ጋር እንዲበቃ ጥቂቶች እየሸረቡ ኢትዮጵያውያንን ዳግም አደጋ ውስጥና ጦርነት ውስጥ እንዳያስገቡ ሕዝባዊ ኢትዮጵያዊና ዜግነታዊ ሚናችሁን እንደትወጡ ለትግራይ ወንድሞቻችንና እህቶቻችን በታላቅ ትህትና አደራ ማለት እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያውያን ተጣልተዋል፤ ይገዳደላሉ፤ ገንዘብ ብናቀብል፣ ሚዲያ ብናቀብል፣ የጦር መሣሪያ ብናቀብል ኢትዮጵያ ትፈርሳለች ብላችሁ ብዙ የተጋችሁ የቅርብና የሩቅ አገራት ኢትዮጵያ የማትፈርስ፣ የፀናች፣ የምትበለፅግ የአፍሪካ ፈርጥና ኩራት ስለሆነች እኛ ኢትዮጵያውያን እያለን ኢትዮጵያን ማፍረስም፣ ማሳነስም፣ በቅኝ መግዛትም የማይታሰብ ስለሆነ ስላወጣችሁት ወጪ፣ ስለድካማችሁ ፈጣሪ ይቅር ይበላችሁ ልላችሁ እወዳለሁ።

በዚህ ጭንቅ ጊዜ ኢትዮጵያን አንጥልም ብለው እጅግ ጥቂት አገራት ለማመን በሚያስቸግር ሁኔታ አንድ አንድ የኢትዮጵያ ክልል ሆነው በመከራ፣ በችግር፣ በጫና፣ ከእኛ ጋር መቆማቸው ብቻ ሳይሆን ያላቸውን ያካፈሉን፣ ጓዳችንን ያበሱ፣ የጓዳችንን መጉደል አይተው የሞሉ፣ ጥቂትም ቢሆኑ አስደማሚ ወዳጆች እንዳሉን ያየንበት ጊዜ ስለሆነ ለነሱ ኢትዮጵያ ታሪክ የምትሠራ፤ ታሪክ የማትረሳ አገር ስለሆነች ብድራታችሁን የምትከፍል መሆኑንና ታላቅ ምስጋና እንዳላት ልገልፅላችሁ እወዳለሁ።

አንተ የተከበርክ፣ ለሕይወትህ የማትሳሳ፣ ሁለት ዓመት ሙሉ በብርድ፣ በዝናብ፣ በየጫካው የተኛህ፣ አንተ የኢትዮጵያ ኩራት፣ የአገር መከላከያ፣ አንተ የኢትዮጵያ ወኔ፣ አንተ የኢትዮጵያዊነት ምልክት፣ አንተ የጀግንነት ምልክት፣ በአንተ ድካም፣ በአንተ መቁሰል፣ በአንተ ሕይወት ኢትዮጵያ ዳግም ቆማ በክብር መናገር ስለቻለች መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ለአገር መከላከያ ያለንን ታላቅ አክብሮትና ፍቅር ካለንበት በመቆም እንድናሰማ በታላቅ ትህትና እጠይቃለሁ። አመሰግናለሁ።

ሰው ይፈጠራል፤ ይኖራል፤ ይሞታል፡፡ ጀግና ግን ይፈጠራል፤ ለልጆቹ አገር ያፀናል፤ እሱ መስዋዕት ይሆናልና እናንተ ጀግኖች ሞታችሁ ሞት አይደለም የደማችሁ መፍሰስም የደም መፍሰስ አይደለም የኢትዮጵያ መፅናት ነውና እንወዳችኋለን፡፡ እናከብራችኋለን፡፡ ክብር ምስጋና ለተሰውት ሰማዕታት እንዲሆን የተቀራችሁ ጀግኖች ክብር እንዲሰማችሁ ለመግለፅ እወዳለሁ።

የጋሞ ሽማግሌዎች ሲመርቁ ‹እንደሚታጨድ ሳር ሳይሆን እንደሚበቅለው ሳር ያለመልምህ› ይላሉ። ኢትዮጵያ እንደሚታጨደው ሳር ሳይሆን እንደሚበቅለው ሳር የምትለምልም፣ የምትበለፅግ የአፍሪካ ኩራት የሆነች፣ የሁላችን መታፈሪያ የሆነች፣ ብርቅዬ አገር፣ ለዚህች አገር አገልጋይ መሆን ሳይሆን ዜጋ መሆንም ትልቅ ክብር ነውና የሚሰማኝን ክብርና ፍቅር ልገልፅላችሁ እወዳለሁ።

በመጨረሻም ከእኛ የተለየ የፖለቲካ እሳቤ ያላችሁ ግለሰቦች፣ ቡድኖች በተከበረው የጋሞ ሕዝብ ፊት ጥሪ ላቀርብላችሁ እፈልጋለሁ። እንኳን በአንድ አገር በአንድ ቤተሰብ ውስጥ ብዙ የማያግባቡ ጉዳዮች አሉ። እንከራከር፤ እንነጋገር፤ እንወያይ፤ ግን የኢትዮጵያን ጥቅም ለታሪካዊ ጠላቶቿ አሳልፈን የምንሸጥ ባንዳዎች አንሁን። ከባለፈው እንማር፤ ብልፅግና የተመረጠው ሕጋዊው የኢትዮጵያ መንግሥት ብቻዬን መንግሥት ካልሆንኩ፤ ብቻዬን ኢትዮጵያን ካልገዛሁ የሚል እብሪት፣ ትዕቢት ያለበት መንግሥት አይደለም።

በመጀመርነው አካታች ክርክርና ወይይት ሁላችንም እንሳተፍ። ለኢትዮጵያ የሚበጅ ሀሳብ እናምጣ። ሕዝባችንን እናወያይና ዳግም መገዳደል፤ ዳግም መሰዳደብ የሌለባት፤ የምትበለፅግ፤ ሰላማዊት ኢትዮጵያን በጋራ እንድንገነባ በታላቅ ትህትና ጥሪ ላደርግላችሁ እፈልጋለሁ።

ኢትዮጵያውያን መሰዳደብ፣ መገዳደል፣ መገፋፋት ይብቃን። ሴት፣ ወንድ፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ አፋር፣ ሱማሌ ሳንል ቤኒሻንጉል፣ ጋምቤላ ሳንል እንደ አንድ ሰው በመካከላችን ያለውን ልዩነት አክብረን ኢትዮጵያን እንድንገነባ፣ እንድናበለፅግ አደራ እያልኩ የኢትዮጵያዊነትን ሽታ፣ የኢትዮጵያዊነትን ጣእም ማወቅ የፈለጋችሁ ወደ ጨዎንቻ እንድትመጡ እጋብዛችኋለሁ።

ይህች ታይታ የማትጠገብ፣ በየቀኑ ምስጢር የሆነች፣ የፈጣሪ ድንቅ ሥራ ተሰጥቶን አደራ መቀበል የማንችል ሕዝቦች እንዳንሆን ልብ እንግዛ፤ ስሜታችንን እንቆጣጠር፤ እንደማመጥ፡፡ ስለ ፍቅር፣ ስለአንደነት፣ ስለብልፅግና ብቻ የምንናገር ይሁን። ከአፋችን፣ ከአንደበታችን የማይረባ ነገር፣ ስድብ ቋንቋ አይውጣ፡፡ ግድየላችሁም ኢትዮጵያ የአፍሪካ ፈርጥ ትሆናለች፡፡ እንደማመጥ፤ እንከባበር፤ በጋራ እንቁም። በዚህ ውይይት ውስጥ ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ማንኛውም ሀሳብ፣ ለኢትዮጵያ የሚበጅ ማንኛውም ሀሳብ ከመጣ ብልፅግና በሁሉም መስክ ዝግጁ መሆኑን በተከበረው በጋሞ ሕዝብ ፊት ቃል ልገባላችሁ እፈልጋለሁ፡፡

ስንዴ፣ አቮካዶ፣ ፓፓያ፣ ሙዝ፣ ቡና፣ ግሪን ሌጋሲ ስንል ቆይተናል፡፡ ዛሬ በምድረገነቷ አርባ ምንጭ የሌማት ቱርፋት ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የሚታወጅበት አዲስ የልማት ዘመቻ በጋራ የምንጀምርበት ስለሆነ አርባ ምንጮች እንኳን ደስ አላችሁ። ለምን አርባ ምንጭን ፈለጋችሁ ከተባለ ልማቱ የሚታይበት፣ ፀሎቱ የሚሰማበት፣ ለምለምና ምድረ ገነት ስለሆነ ነው። ጋሞዎች ስለፍቅራችሁ፣ ስላሳያችሁን ትህትና፣ ስለልጆቻችሁ መስዋእትነት፣ ኢትዮጵያ ለዘላለም ታከብራችኋለች።

እኔም ልጃችሁ ወንድማችሁ እጅግ አድርጌ አመስግናችኋለሁ። ሰላም ለኢትዮጵያ! ሰላም ለአፍሪካ! ሰላምና ብልፅግና ለመላው ዓለም ይሁን። ኢትዮጵያ በልጆቿ ጥረት ታፍራና ተከብራ ለዘለዓለም ትኑር። ፈጣሪ ኢትዮጵያና ልጆቿን ይባርክ። አመስግናለሁ።

# የሠርግ ዐጸዱ ሠርግ

ግርማ መንግሥቴ



ሙሽሮች

**የኛማ ሙሽራ (2 ጊዜ)**
**እጹብ ድንቅ ስራ**
**በሆታ በእልልታ እንቀበላቸው**
**ሙሽሪት ሙሽራው ዛሬ ነው ቀናቸው።**

“ሠርግ”ን የደስታ ተክለወልድ መዝገበ ቃላቱ “ለአካለ መጠን የደረሰ ወንድ ልጅና ለአካለ መጠን የደረሰች ሴት ልጅ ባልና ሚስት ሊሆኑ የሚጋቡበት ቀንና ሠርግ፤ ተጋብተውም የዚህን ዓለም ኑሮ የሚጀምሩበት የሠርግ ቀን።” በማለት የሚፈታው ሲሆን፣ እኛም ይህንኑ ብያኔ ይዘን ሀሳብ መለዋወጣችንን እንቀጥላለን።

ሠርግ እንደው ዝም ብሎ ሰዎች ለአካለ መጠን ስለ ደረሱ ብቻ የሚደረግ ሳይሆን ኃይማኖታዊ መሰረት ያለ ሰብአዊ ተግባር ሲሆን፣ የሚከተሉት አናቅፅ የሚነግሩንም ይህንን ነው።

መንግሥተ ሰማያት ለልጁ ሠርግ ያደረገ ንጉሥን ትመስላለች። (የማቴዎስ ወንጌል ምዕራፍ ፳፪ (22)፣ ቁጥር ፪ (2)

በሦስተኛውም ቀን በቃና ዘገሊላ ሰርግ ነበረ፤ የኢየሱስም እናት በዚያ ነበረች፤ ኢየሱስም ደቀ መዛሙርቱም ወደ ሠርጉ ታደሙ። (የዮሐንስ ወንጌል ምዕራፍ ፪ (2)

ከእነዚህ ከታላቁ መጽሐፍ ቅዱስ (በሌሎች ኃይማኖቶችም የሚኖር ይመስለናል) ጥቅሶች የምንረዳቸው በርካታ ቁም ነገሮች ያሉ ሲሆን፤ የሠርግን አስፈላጊነት፣ የሠርግ ደጋሽን ከፍታ ቦታ፣ ሠርግ የሚሠረግበት ቦታ ክቡርነትን እንረዳለን። ከዚህ አኳያ በመናፈሻው የተጋቡት ጥንዶች እድለኞች ሆነው እናገኛቸዋለን።

በእግዚአብሔር ዘንድ ሠርግ ከልብሱ ጀምሮ ልዩ ቦታና ክብር አለው። የስራ ልብስ እንዳለ ሁሉ፤ የሠርግም ልብስ አለ። ለዚህም “የሠርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደ’ዚህ ገባህ? አለው፤ እርሱም ዝም አለ።” የማቲዎስ ወንጌል ምእራፍ ፳፪ (22)፣ ቁጥር ፲፪ (12) የሚለው ብቻ በቂ ማመሳከሪያ ነው።

“እናቱ በሠርጉ ቀንና በልቡ ደስታ ቀን ያደረገችለትን አክሊል ደፍቶ ንጉሥ ሰሎሞንን እዩ።” (መኃልየ መኃልይ ዘሰሎሞን ምዕራፍ 3፣ ቁጥር 11) የሚለውም እንደዚሁ ከሠርግ አልባሳት፣ ውበትና ውድነት ጋር የተያያዘ ነውና ሠርግ የዋዛ ትርጓሜ ያለው ጉዳይ አይደለም።

የሠርግ ጥሪውም ሆነ ስፍራው (አዳራሹ ወይም “የሠርግ ቤት” በሚል የሚታወቀው) ልዩ ክብር አለው። መጽሐፉ “ማንም ለሠርግ ቢጠራህ በከበሬታ ስፍራ አትቀመጥ፤ ምናልባት ከአንተ ይልቅ የከበረ ተጠርቶ ይሆናልና …” (የሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ ፲፬ (14)፣ ቁጥር ፰ (8) እንደሚለው ሠርግ የተከበሩ፣ ለሠርገኛው የቀረቡ … ሰዎች የሚታደሙበት እንጂ እንደ መሸታ ቤት ማንም የሚዋከብበት ስፍራ አይደለም። ወደ መሬት እናውርደው።

ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ከሆኑት አንዱ ሠርግ ነው። በየትኛውም ዓለም ሠርግ አለ። እንደየባህሉ፣ አድባርና አውጋሩ በየትም ስፍራ ሰው ይዳራል፤ ይሠረጋል። የቁጥርና አንዳንድ ልዩነቶች ካልሆኑ በስተቀር በየትኛውም አገር ሙሽራ አለ፤ የትም ቢኬድ ሠርገኛ አለ። ይበላል፤ ይጠጣል … ወዘተርፈ። እኛም አገር የሚሆነው፣ እየሆነም ያለው ይኸው እንጂ ሌላ አይደለም።

ምንም እንኳን ጥር “የሙሽሮች ወር” ከሚለው ወጣ ያለ ቢመስልም፤ ያለ ምንም የኃይማኖት ልዩነት በአንድ መሞሸር በራሱ የሚፈጥረው ስሜትም ሆነ፣ የሚያስገኘው ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳ በቀላሉ የሚታይ አይደለም። በነበረን አገራዊ እሴት ላይ ሌላ አገርኛ ጨመርን ማለት ይኸው ነው። አሁን የዚህ ጽሑፍ መነሻ ወደ ሆነው ጉዳያችን እንምጣ።

ከቻይና መንግሥት በተገኘው ድጋፍ ሸገርን የማስዋብ ፕሮጀክት አንድ አካል የሆነው ስፍራ መልማት ከጀመረ በኋላ በዘመናዊ መልክ የተገነባው የወዳጅነት ፓርክ (ፍሬንድሺፕ ስኩዌር) ጳጉሜ 5 ቀን 2012 ዓ.ም ተጠናቆ ለሕዝብ ክፍት መሆኑ ይታወሳል።

የዚሁ ፕሮጀክት አካል የሆነው ሁለተኛው ምዕራፍ ባለፈው እሁድ (ጥቅምት 20 ቀን 2015 ዓ.ም) ተመርቆ ለሕዝብ ክፍት ሆኗል።

የሸገር ፕሮጀክት ምዕራፍ ሁለት መጠናቀቁን በማስመልከት፣ “ለምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ልዩ ስጦታ” ይሆን ዘንድ ለአዲስ ተጋቢ ሙሽሮች ልዩ ስጦታ ቀርቧል። ስጦታውም፡-

**የፓርኩ ምርቃት በሆነው የወዳጅነት የሠርግ ዐጸድ ላይ 50 ጥንዶች የጋብቻ ሥነ ሥርዓታቸውን አከናውነዋል**

“ጋብቻቸውን ለመፈጸም የተዘጋጁ ወይም አቅደው ሳይሳካላቸው የቆዩ 50 ጥንዶችን በመሥፈርት መርጦ የጋብቻ ሥርዓታቸውን በሥፍራው እንዲፈጽሙ ታቅዷል። በመሆኑም መሞሸር ያሰቡ ወይም ሊሞሸሩ አቅደው በልዩ ልዩ ምክንያት ሳይከውኑት የቀሩ፣ በዚህ ዘመናዊ እና ያማረ ስፍራ ሠርጋቸውን ከሚፈጽሙ 50 ጥንዶች መካከል እንዲሆኑ ጥሪ ቀርቧል። በፕሮጀክቱ ምረቃ ዕለት ሠርጋቸው ከሚፈጸም 50 ጥንዶች አንዱ ለመሆን የሚከተለውን ቅጽ ሞልተው እስከ ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም ከቀኑ 6፡00 ሰዓት ድረስ በshegerprize@pmo.gov.et ኢሜይል በመላክ እንዲሳተፉ”

የሚለውን ባካተተ መልኩ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የፌስቡክ ገፅ አማካኝነት ለመላው ህዝብ ተሰራጭቷል። በዚሁ መሰረትም የሚመለከታቸውና በሠርግ ዐጸዱ መሞሸር የፈለጉ ተመዝግበዋል። በወጣው መስፈርት መሰረት ተወዳድረው ያለፉት 50ዎቹ የልዩ ስጦታው ተጠቃሚ ሆነዋል።

የፓርኩ ምርቃት በሆነው የወዳጅነት የሠርግ ዐጸድ ላይ 50 ጥንዶች የጋብቻ ሥነ ሥርዓታቸውን አከናውነዋል። በአዲስ አበባ ከተማ (ከባሻ ወልዴ ችሎት እስከ አራ በከንቱ ባለው ስፍራ) የተገነባው የሸገር ፓርክ ሁለተኛ ምዕራፍ ፕሮጀክት የተለያዩ የሕፃናት መዝናኛዎችን፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ስፍራዎችና የኪነጥበብ ዝግጅት ማሳያዎችን፣ ካፌና ሬስቶራንቶችን … ይዟል። በተጨማሪ የተለያዩ ሁነቶች የሚስተናገዱባቸውን ዘመናዊ አዳራሾችንና ማዕከላትን የያዘ መሆኑንም መመልከት ተችሏል። የሸገር ፓርክ ሁለተኛ ምዕራፍ ሕፃናት ባህልና ታሪካቸውን እያወቁ የተለያዩ ዕውቀቶችን የሚቀስሙበት ዘመናዊ የሕፃናት መዝናኛና ሰብእና መገንቢያ ማዕከልንም ያካተተ ነው።

በምረቃው እለት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤

ለቀጣዩ የአገራችን ዕድገት መሠረት ለመጣል ልጆች ላይ ትኩረት አድርገን ከአሁኑ መሰራት ያለበት መሆኑ፤ በተለያዩ ቦታዎች ላይ አሁን የሚታየው ችግር ልጆች ላይ ካለመሥራት የመጣ እንደሆነ፤ መንግስታቸው የተሻለች አገር ለመገንባት መሠረቱ ላይ ትኩረት አድርጎ መስራቱን የሚቀጥል መሆኑን፤ በቀጣይ አገራዊ ግንባታ በአዕምሮና በሥነልቦና የዳበረ ትውልድ ለመገንባት ጥረት ማድረግ እንደሚገባ፤ ልጆች አገራቸውን እያደነቁና እየወደዱ ጊዜያቸውን ማሳለፍ ከቻሉ በቀጣይ ለአገር ግንባታ ያላቸው ጠቀሜታ ከፍተኛ እንደሚሆን፤ አገር የሚመሠረተው በጠንካራ ትውልድ መሆኑ፤ ጠንካራ ትውልድ ያላት አገር ችግሮችን ተቋቁማ ማለፍ የማትቸገር ስለመሆኗ፤ ትውልዱ ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት ከተቻለ የበለጠ ፍሬያማ መሆን እንደሚቻል፤ በዚህ አግባብ በሺዎች የሚቆጠሩ የሕፃናት ቅድመ ትምህርት ቤቶች የተገነቡ መሆናቸውን፤ እንዲሁም፣ በፓርኩ ውስጥ የሚዝናኑ ልጆች በዘመናዊ መንገድ እንዴት ፈተናዎችንና ችግሮችን ማለፍ እንደሚችሉ እየተማሩ አካላቸውንና አዕምሯቸውን ማዳበር የሚችሉ ስለ መሆናቸው ወዘተ መናገራቸውም የዚሁ አካል ነው።

የፕሮጀክቱን መጠናቀቅና የምረቃ ስነስርአቱን አስመልክቶ የጠቅላይ ሚኒስትሩ ጽሕፈት ቤት በሰጠው መረጃ እንዳመለከተው፣ አዲስ አበባን ለኑሮ ምቹ ለማድረግ እና ለስሟ የሚመጥን ገጽታ እንዲኖራት ታልሞ ሲሠራ የቆየው የሸገር ፕሮጀክት ምዕራፍ ሁለት በስኬት ተጠናቋል።

ለሀገር ኩራት፣ ለጎብኚዎች መዳረሻ፣ ለመዲናችን ነዋሪዎች የዘወትር መገልገያ እንዲሆን የተዘጋጀውና የሸገርን ማስዋብ ፕሮጀክት አካል የሆነው ሁለተኛ ምዕራፍ ለአገር ኩራት መሆኑም በእለቱ ተገልጿል። በተሰራጨው ጽሑፍ ላይም ተመልክቷል።

በአገር በቀል እፅዋት የተዋበው ፓርክ የሚገኝበት ስፍራ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ፊት ለፊት አንስቶ ወደ አሮጌው ቄራ መውረጃና አራ በከንቱ ወንዝን ተሻግሮ (ዘመናዊ ድልድይ ተሰርቶለታል) የሚዘልቅ ሲሆን፤ ፓርኩ ከመገንባቱ በፊት “አካባቢው ለልማት …” በሚል ፈርሶ ከ10 ዓመት በላይ ስፍራው ያለ አገልግሎት ተቀምጦ የነበረ መሆኑ ይታወቃል። (በነገራችን ላይ፣ የአካባቢውን የ“ድሮና ዘንድሮ” ገፅታና ንጽጽር ለመግለፅ ልዩ ችሎታን የሚጠይቅ መሆኑን እዚህ ላይ ሳይናገሩ ማለፍ ይከብዳል።)

ከላይ እንደገለፅነው፣ የወዳጅነት ፓርክ ምዕራፍ ሁለት የሕፃናትና ወጣቶች መዝናኛ ፓርክ መጠናቀቅ ጋር በተያያዘ፣ በምዕራፍ ሁለት ፕሮጀክቱ የምረቃ ሥነ ሥርዓቱ ዕለት ጋብቻቸውን ለመፈጸም የተዘጋጁ ወይም አቅደው ሳይሳካላቸው የቆዩ 50 ጥንዶችን በመሥፈርት መርጦ የጋብቻ ሥርዓታቸውን በሥፍራው እንዲያከናውኑ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ማስታወቁ ይታወሳል። በዚሁ መሰረትም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይና ሌሎች ከፍተኛ ባለስልጣናት በተገኙበት ጋብቻው ተካሂዷል።

በእለቱም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አህመድ ከባለቤታቸው ቀዳማዊት እመቤት ዝናሽ ታያቸው ጋር በመሆን ኬክ የቆረሱ ሲሆን፤ “የወዳጅነት ፓርክ ምዕራፍ ሁለትን በከፈትንበት ዕለት በሠርግ ዐጸዱ ጋብቻችሁን የፈጸማችሁ ሁሉ እንኳን ደስ አላችሁ” በማለት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ የሙሽሮቹና እድምተኞቹ የደስታ ተካፋይ ሆነዋል። “ጋብቻ የሀገር መሠረት ከሆኑት ተቋማት አንዱ የሆነው ቤተሰብ የሚመሠረትበት ነው። ኢትዮጵያውያን በሀገራችን፣ ሌሎችም ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ዓለም አቀፍ፣ ሀገራዊ እና ማኅበራዊ ክንውኖች የሚፈጸሙበትን ድንቅ ስፍራ በሠርጋችሁ ደስታ አድምቃችሁ አስጀምራችሁታል።” ሲሉም የአፀዱን የአሁንና የወደፊት ፋይዳ አመላክተዋል።

ከሠርጉ ፕሮግራም አስቀድሞ፣ ማለትም በጠዋቱ የልጆች መዝናኛ ስፍራው ምርቃት ፕሮግራም ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ያስተላለፉት መልእክት ያለ ሲሆን፤ ከመልእክቶቻቸውም ዋና ዋናዎቹም፣

ተመሳሳይ ፕሮጀክቶችም በየክልሎቹ መገንባትና ቀጣዩ ትውልድ ላይ መሥራት እንደሚያስፈልግ፤ ፈተናዎችን የሚቋቋም ጠንካራ ትውልድ መገንባት የሚቻለው ከታችኛው የዕድሜ ክልል አንስቶ እንደ ሆነ፤ ለዚህ ደግሞ ሕፃናት ማንበቢያ፣ ማሰቢያ፤ እንዲሁም፣ አካላዊና አዕምሯዊ ብቃታቸውን የሚያዳብሩባቸው ስፍራዎች በብዛት የሚያስፈልጉ መሆኑን፤ መንግሥትም በርካታ የሕፃናት መዋያዎችንና ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ላይ እንደሚገኝ፤ ከዚህ ባለፈ ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ጋር በተያያዘ ዘጠኝ ሚሊዮን ሕፃናትን መመገብ የተቻለ ስለመሆኑ፤ ከመዋዕለ ሕፃናትና አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከተከናወኑ ሥራዎች ባለፈ እንደ ወዳጅነት ፓርክ፣ ምዕራፍ ሁለት ዓይነት ፓርኮች ለትውልድ ግንባታ ያላቸው ሚና ከፍተኛ መሆኑን፤ ፓርኩ በከተማዋ መሃል የሚገኝና ዜጎች ልጆቻቸውን ለማዝናናት ሲፈልጉ በቅርበት የሚያገኙት ደረጃውን የጠበቀ ስፍራ መሆኑና ይህም ተመራጭ እንደሚያደርገው፤ የወዳጅነት ፓርክ ሁለተኛው ምዕራፍ ስፖርትን፣ ጨዋታንና ማኅበራዊ መስተጋብርን … ያቀናጀ ስለመሆኑ፤ ልጆች እየተጫወቱ ሳይንስና ቴክኖሎጂን እንዲተዋወቁ፣ እንዲያነቡ፣ ስፖርት እንዲሰሩ … መልካም አጋጣሚን የሚፈጥርላቸው ስለመሆኑ፤ ወላጆችና አያቶች ከልጆቻቸው ጋር መጥተው ማኅበራዊ ልምዳቸውን የሚለዋወጡበት ስፍራ እንደሚሆን፤ አዲስ ተጋቢዎች በሠርግ ዐጸዱ ጋብቻቸውን የሚመሰርቱ መሆናቸው፤ ይህም በበኩሉ የነገዋ ኢትዮጵያ የተሻለች እንድትሆን የተሻለ ትውልድ እያፈራን እንድንቀጥል መሰረት ስለመሆኑ … ከተናገሩት ይገኙባቸዋል።

የወዳጅነት ምዕራፍ ሁለትን ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል ለአንድ ሳምንት በነፃ መጎብኘት የሚችል መሆኑንም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ያስታወቁት በዚሁ ወቅት ነበር።

በመጨረሻም፣ በሠርግ አፀዱ ለተጋቡት በሙሉ መልካም የትዳርና የሕይወት ዘመን እንዲሆንላቸው እየተመኘን፤ “እንደዚህ አይነት ማእከላት ይብዙልን!!!” እንላለን።

ማህበራዊ

# ወጣቶች

## የወጣቶቹ ጀብዱ በጦር ሜዳ


አስር አለቃ አብርሃም

አስናቀ ፀጋዬ

ይህን ቀን ማንም ኢትዮጵያዊ አይረሳውም።አዎ! ይህ ቀን የሀገር ባለውለታ፣ የብዙዎች አለኝታና የሀገር ዳር ድምበር ጠባቂ የሆነው እንቁው የሀገር መከላከያ ሰራዊት በሀገር በቀል ባንዳዎች ከጀርባው የተወጋባት ቀን ነው።ሰራዊቱ ለዛ ሀገር ህዝብ ስንት ነገር እንዳላደረገ ተከዶ በግፍ የተጨፈጨፈበት ቀንም ነው።

ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ጥቁር ታሪክ የተጻፈበት ቀን ነው።ሀገሪቷን ለሃያ ሰባት አመታት በብሔር ከፋፍሎ የራሱን ጥቅም ብቻ እያጋበሰ ሲያስተዳድራት የነበረው አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በእስኪርቢቶ ተሸንፎ የአራት ኪሎ ቤተመንግስትን ተሰናብቶ መቀሌ ከተሸኘ በኋላ እኔ ያልገዛኋት ሀገር ትፍረስ በሚል ለሃያ አመታት በቀበሮ ጉድጓድ ውስጥ ሆኖ ሲጠብቀው የነበረውን የሀገር መከላከያ ሰራዊት ከጀርባው የወጋበት ቀን ነው።

በዚህ ድንገተኛ ጥቃት ከሀዲ ቡድኑ ብዛት ያላቸው የመከላከያ ሰራዊት አባላትን በግፍ ጨፈጨፈ።አብዛኛዎቹን ከባድ መሳሪያዎችም በእጁ ካስገባ በኋላ ከኔ በላይ ማንም የለም አለ።መከላከያ ሰራዊቱን መንካት ኢትዮጵያን መንካት ነውና ጠቅላይ ሚንስቴር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ ጥቃቱ ከተከሰተ በኋላ ንጋት ላይ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ቀርበው ስለድርጊቱ አብራርተው የአፀፋ እርምጃ እንዲወሰድ ትእዛዝ አስተላለፉ።

ወትሮም ኢትዮጵያ ስትነካ የማይወደው የሀገር መከላከያ ሰራዊት ከደረሰበት ጥቃት ዳግም አገግሞ ለሀገሪቷ ሉዓላዊነትና ለመላው ኢትዮጵያውያን ሲል ወደ ጦርነቱ ገባ።በግዜው ሰራዊቱ ወደ ጦርነቱ ሲገባ እጁ ላይ ብዙም የጦር መሳሪያ አልነበረውም።ሆኖም ባለው መሳሪያ ራሱን አደራጅቶና ህዝቡን ደጀን አድርጎ አሸባሪ ቡድኑን ገጠመ።

ቀድሞም የተገፋችው ኢትዮጵያ ናትና ሰራዊቱ ለኢትዮጵያና ለህዝቧ ሲል ሀቅን ይዞ ወደ ጦርነቱ በመግባቱ በድል ላይ ድል ይጎናፀፍ ጀመር።በጥቂት ጊዚያት ውስጥም አብዛኛዎቹን የጠላት ታጣቂዎችንና ይዞታዎችን መደምሰስ ቻለ።በጠላት ይዞታ ስር የነበሩ ከባድ መሳሪያዎችንም አብዛኞቹን ደምስሶ ጥቂት የማይባሉትንም ማረከ።በዚህ ግስጋሴውም እለት በእለት ድል እያገኘ ጠላትን ገሚሱን ደምስሶ ገሚሱን ደግሞ ማርኮ ሶስት ሳምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ መቀሌን ተቆጣጠረ።

ሰራዊቱ መቀሌ ከገባ በኋላ ህዝቡን የማረጋጋት፣ የመጠበቅና ሌሎችንም ስራዎች ሲያከናውን የቆየ ቢሆንም ጥቂት የአሸባሪው ቡድን ደጋፊዎች መረጃ እየሰጡ ከኋላው ለማስወጋት በተደጋጋሚ ሞክረዋል።በዚህም ጥቂት በማይባሉ የሰራዊቱ አባላት ላይ ሞትና መቁሰል ተከስቷል። በዚህም መንግስት ቢያንስ ህዝቡ የጥሞና ጊዜ ይሰጠው፤ እርሻም ይረስ ብሎ ሰራዊቱን ከትግራይ ክልል ሙሉ በሙሉ አስወጣ።

ድሮም የጦርነት ልክፍት ያለበት አሸባሪ ቡድኑ ከወራት በኋላ በክረምት ወቅት ጊዜው ባለፈበት የጦርነት ታክቲክ ከህፃናት እስከ አዛውንት በማሰለፍ በህዝብ ማዕበል የአማራና አፋር አጎራባች አካባቢዎችን መውረር ጀመረ።የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊትም የከፋ የህዝብ እልቂት እንዳይከሰት ወደኋላ አፈገፈገ።ለዚህ ኃይል የሚመጥን ሰራዊት መገንባት እንደሚያስፈልግም መንግስት አመነ።

ጠቅላይ ሚንስትር ዶክተር ዐቢይ ወጣቱ የመከላከያ ሰራዊትን እንዲቀላቀል ያቀረቡትን ጥሪ ተከትሎ ማህፀነ ለምለሟ ኢትዮጵያ ልጆቿን ለሰራዊቱ በፍቃደኝነት እንካችሁ አለች።ሰራዊቱን በየጊዜው የሚቀላቀለው የወጣት ቁጥርም ማእበል ሆነ።ሰራዊቱም በመሳሪያና በሰው ኃይል ይበልጥ ተደራጀ።የህዝቡ ደጀንነትም ይበልጥ ተጠናከረ።በዚህ ጊዜ አሸባሪ ቡድኑ ወረራውን አጠናክሮ ደብረሲና ደርሶ የነበረ ቢሆንም በኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ተደምስሶ ወደመጣበት ተመለሰ።

ቡድኑ የሞት ሽረት አድርጎ ለሶስተኛ ዙር ወረራ በቅርቡ ቢነሳም ህልሙ ሊሳካለት አልቻለም።እለት በእለት በጥምር ኃይሉ በሚደርስበት ድቆሳ አቅሙ ተዳክሞ ጀምበር አዘቅዝቃበታለች።በራሴ ሜዳ እየተዋጋው እስከመጨረሻው እዝልቃለሁ ብሎ ቢፍጨረጨርም አልሆነለትም።በነዚህ ሁሉ ተጋድሎ ታዲያ አብዛኛዎቹ ወጣት የመከላከያ ሰራዊት አባል ጠላትን እየተፋለሙና መስዋት እየከፈሉ በታላቅ ጀብዱ የሀገራቸውን ሉዓላዊነት አስከብረዋል።በትውልድ ቅብብሎሽ ሀገር እንደምትፀናም አስመስክረዋል።

መቼም ዝክረ ሰሜን እዝ ሲወሳ ወጣቷ አስር አለቃ በላይነሽ ደባልቄ የፈፀመችውን ጀብድ መዘንጋት አይገባም። 20ኛ ቃሉ ክፍለ ጦር ሰሜን ዕዝ ካሏት የጦር ክፍሎች ውስጥ አንዱ ነው። በዚህ ክፍለ ጦር አንደኛ ብርጌድ አንደኛ ሻለቃ አባል የሆነችው ምክትል አስር አለቃ ገበያነሽ ደባልቄ የሻለቃው አዛዥ ኮሎኔል ሰለሞን ገብረ ዮሃንስ አጃቢ ብትሆንም ሰውየው ጁንታ መሆኑን ግን አታውቅም።

አሸባሪ ቡድኑ የእብሪት እርምጃቸውን ከመጀመሩ ከሶስት ቀናት በፊት ሰራዊቱ የምግብና መጠጥ አገልግሎት የሚያገኝባቸውን መንገድ በመዝጋት ለከፍተኛ ርሃብና ጥም ዳርጎታል። በጊዜው ቡድኑ ሁሉም የሰራዊት አባል የግል ትጥቁን በአንድ ክፍል በማስቀመጥ በህብረተሰብ የድጋፍ ስራዎች ላይ እንዲረባረብ አደረገ።

በተለይም ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ምሽት ላይ ሁሉንም የጥበቃ ቦታዎች በትግራይ ተወላጅ የሰራዊት አባላት እንዲሸፈኑ በማድረግ፣ የከሃዲው ቡድን ልዩ ኃይልና ሚሊሻ ምንም አይነት ዝግጅትና ትጥቅ ባልነበረው ሰራዊት ላይ ከፍተኛ ተኩስ ከፈተ። ሆኖም ታላቅ ጀግንነትና ኢትዮጵያዊ ማንነትን የወረሰው ጀግናው የመከላከያ ኃይል የማይታሰቡ ጀብዶችን ጭምር በመፈፀምና ወደ ኤርትራ በመሸሽ ራሱን ማዳን ችሏል።

በዚህ ሁሉ ግፍና በደል መሃል የሻለቃዋ ዋና አዛዥና ለዘመናት የመራቸውን የሀገር መከላከያ ሰራዊት አባላት የካደው ኮሎኔል ሰለሞን ገብረ ዮሃንስ ራሱን መፀዳጃ ቤት ውስጥ በመደበቅ በጁንታው የተሰጠውን ተልዕኮ መፈፀም እንደጀመረ አስር አለቃ ገበያነሽ ሁኔታውን በንቃት ትከታተል ነበር።

ውትድርና በኢትዮጵያዊነት ፍቅር መታጠብና በጀግንነት ካባ መድመቅ መሆኑን ጠንቅቃ የምታውቀው እንስቷ ጀግና ፣ ራስን ለሀገር አሳልፎ መስጠት ታላቅ ኢትዮጵያዊነት መሆኑንና ይህም ብቻውን ጀግንነትን እንደሚወልድ በመረዳት ከሀዲውን ኮሎኔል ከስሯ እንዲንበረከክ አድርገዋለች።

"ሰራዊታችን በታፈነበት ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ምሽት 2 ሰዓት ላይ በከባድ መሳሪያ የታጀበ ተኩስ ወደ ካምፓችን ተተኮሰ፣ በዚህ ሰዓት ወደ መፀዳጃ ቤት ራሱን ለተደበቀው ካሃዲው አዛዥ ተብዬ እኔ በትግራይ ሚሊሻና ልዩ ኃይል ጥይት ከምሞት አንተን ገድዬ ራሴን አጠፋለሁ አልኩት» ስትል በጊዜው የተፈጠረውን ሁኔታ አስረድታለች።

«ተኩሱ በርትቷል፣ ሁሉም ራሱን ለማዳን ወደሀሊናው የመጣለትን አማራጭ እየተጠቀመ ይሯሯጣል።በመጨረሻም ኮሌኔሉ ከተደበቀበት መፀዳጃ ቤት እንዲወጣና እኔ የምለውን ብቻ እንዲፈፅም እሺ የማይል ከሆነ ግን እንደምገድለው አስጠነቀቁት» ትላለች ምክትል አስር አለቃ ገበያነሽ ክስተቱን ስትተርክ።

እሱም በፍርሃት ውስጥ ሆኖ ከተደበቀበት ቦታ ወጥቶ ወደነገርኩት ቦታ መጣ።ሽጉጡንና ማዕረጉን እንዲሰጠኝ አደረኩ።ከዛም ጫማውን እንዲያወልቅ አድርጌ በየመንገዱ ከማገኛቸው የሰራዊት አባላት ጋር በመተባበርና ሙሉ ሌሊት የእግር ጉዞ በማድረግ ኤርትራ ይገኘው በመግባት ታማኝ እና ሙሉ ኢትዮጵያዊ ለሆኑ አመራሮች አስረከብኩት" ስትል አውግታለች።

ሰራዊቱ በራሱ ወገኖች የደረሰበትን በቃላት የማይገለፅ ግፍና በደል ተሸክሞ ቂምን ሳይሆን ኢትዮጵያዊ ፍቅርን አስቀድሞ ለድል በመብቃቱ ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማትም ምክትል አስር አለቃ ገበያነሽ ደባልቄ ስሜቷን አጋርታለች።

ሌላኛው ወጣት ባለጀብዱ አስር አለቃ ጌታቸው ገዛኸኝ ሲሆን ከደቡብ ክልል ከፋ ዞን የበቀለ የመከላከያ ሰራዊት አባል ነው።የመከላከያ ሰራዊቱን የተቀላቀለውም በ2009 ዓ.ም ነው።ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተሰጠውን ሀገራዊ ተልእኮ ተቀብሎ ሲፈፅም ቆይቷል።አሸባሪው የሕወሓት ቡድን በከፈተው ወረራ ቡድኑን ለመደምሰስ በተካሄደው የህልውና ዘመቻ ተፋልሞ ጠላትን ድባቅ መቷል።

በተለይ ከሰሜን ወሎ በኩል ብርቱ ክንድ ያረፈበት አሸባሪ ቡድኑ በወረባቦ በኩል የደቡብ ወሎ አካባቢዎችን ለመውረር በሚፍጨረጨርበት ጊዜ ወጣቱ አስር አለቃ ጌታቸው ገዛኸኝ ከጠላት ጋር ፊት ለፊት ተናንቆ በያዘው ክላሽ በመደምሰስ አምስት ስናይፐሮችን ከነሙሉ ትጥቅ ማርኳል።አርባ ስምንት የአሸባሪ ቡድኑ ታጣቂዎችንም ደምስሷል።

አስር አለቃ ጌታቸው ገዛኸኝ ተቅበዝብዞ የመጣውን አሸባሪ ቡድን ድባቅ በመምታት አምስት ስናይፐር ብቻ ሳይሆን የማረከው የጠላት ብሬል እንዳይሰራ በማድረግ ተጨማሪ ጀብድ ፈፅሟል።

በወረባቦ በኩል በነበረው አውደ ውጊያ ታላቅ ጀብዱ ከፈፀመው አስር አለቃ ጌታቸው ገዛኸኝ ጋር አብሮ በግንባር ሲፋለም የነበረው ጓደኛው አስረስ ማሙሽ «አምስት የቡድን መሳሪያ ጠምደን እየተታኮስን እያለ እርሱ ለብቻው ግራና ቀኝ እያስተባበረ ነበር» ይላል። የእነርሱ ብሬል ተኳሽና ሬዲዮ ኦፕሬተር እየመጡ ሳለ በዚሁ መሀል አምስት ስናይፐር የታጠቁትን በተከታታይ በክላሽ በመግደል መሳሪያዎቹን መማረኩን ይናገራል። ብሬላቸው እንዳይሰራም ዋናውን መውጊያ እንደሰበረውም ይገልፃል።

ወታደርነት ስለሀገር ፍቅር መስዋትነት የሚከፈልበት ከራስ በላይ ለወገን ክብር ዘብ የሚቆምበት ታላቅ ሙያ እንደሆነም ነው አስር አለቃ ጌታቸው ገዛኸኝ የሚናገረው።«ከራስ በላይ ሀገርና ወገንን ነው የምንጠብቀውም» ይላል በታላቅ የሀገር ፍቅር ስሜት።

በሌላ በኩል ደግሞ ምክትል መቶ አለቃ ኤርሚያስ ማቲዎስ በሰራዊቱ የሚሰጡትን ግዳጆች በውጤታማነት በመፈፀም ታላቅ ታሪክ ካስመዘገቡ ወጣት የመከላከያ ሰራዊት አባላት ውስጥ አንዱ ነው።አሸባሪ ቡድኑ በከፈተው ጦርነት በሻምበል አመራርነት ጦሩን በመምራት ምሽግ በመስበርም ታላቅ ጀብዱ ፈፅሟል።በትግል ላይ እያለ ቢቆስልም ወደኋላ ሳይል ለሀገሩ የገባውን ቃልኪዳን በተግባር አረጋግጧል።

እርሱ ቢቆስልም ሲመራት የነበረችው ሻምበል ወኔውን አይታ ካለችበት ቦታ ለአራት ቀናት ሳትነቃነቅ አሸባሪ ቡድንኑ ተፋልማ ምሽጉን አስለቅቃለች። እርሱም ቁስሉን ችሎ ከሻምበሏ ጋር አብሮ ቆይቶ ትልቅ ጀብዱ ፈፅሟል።

«ያለን አንድ ሀገርና አንድ ሕይወት ነው» የሚለው ምክትል መቶ አለቃ ኤርሚያስ፤ የማይተካ ሕይወታችንን ለሀገራችን ስንል እንከፍላለን ሲል በወኔ ይናገራል።አባቶቻችን መስዋትነት ከፍለው ያሻገሯትን ሀገራችንን ኢትዮጵያ እኛ ወጣቶችም መስዋት ከፍለን ሀገራችንን ማሻገር ይጠበቅብናል ይላል።ለዚህም ታዲያ ወጣቱ የመከላከያ ሰራዊት አባል በመሆን የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ማስጠበቅ እንዳለበት መልእክቱን ያስተላልፋል።

ሌላው በዚህ የህልውና ዘመቻ ጀብድ ከፈፀሙ ወጣቶች ውስጥ አንዱ የመከላከያ ሠራዊት አምስተኛ ሜካናይዝድ ክፍለ ጦር አባል ቁመተ መለሎው 10 አለቃ አብርሃም ነው። በመከላከያ ሠራዊት ውስጥ ከስድስት ዓመታት በላይ አገልግሏል።

አስር አለቃ አብርሃም የሚያሽከረክራትን ታንክ ልክ እንደ እጁ መዳፍ ያውቃታል።በጋሸና እና ደብረዘቢጥ ግንባሮች ላይ የአገሬን ንብረት ለጠላት አሳልፌ አልሰጥም በሚል እልህ አስጨራሽ ተጋድሎ አድርጓል።

በውትድርና ቆይታዬ ሁሉ እንደ ደብረዘቢጥ እና ጋሸና ያህል ፈታኝ ቀናትን ያሳለፍኩበት ወቅት የለም፤ ይሁንና ከጓዶቼ እና ደጀን ሕዝቡ ጋር በመሆን ወራሪውን አሳፍረነዋል፤ በደብረዘቢጥም ሆነ በጋሸና ግንባር አኩሪ ድል አስመዝግበናል ሲል ይገልጻል።

አስር አለቃ አብርሃም ከጋሳኝ አንስቶ እስከ ደብረዘቢጥ በነበረው ውጊያ ላይ ታንክ እያሽከረከርኩ ግንባር ላይ ሲዋጋ ነበር። በወቅቱ ሃሸሽ የወሰዱ የአሸባሪው ሕወሓት ቡድን ታጣቂዎች ታንኩ ድረስ መጥተው በብሬል እና በተለያዩ መሳሪያዎች ታንኩ ላይ ጥይት አዘነቡ።

በድንገት ግን የሽብር ቡድኑ ታጣቂዎች የታንኩን መነፅር መቱበት። የታንኩን የተለያዩ ክፍሎች ማበላሸታቸውንም ቀጠሉ። በቅርበት መጥተውም ከበቡት። ይሁንና ድፍረት አልባ በመሆናቸው ታንኩ ላይ ወጥተው ለመያዝ እንኳን ወኔ አልነበራቸውም።

እሱም የታንክ መነጸሩ ቢሰበርበትም ለጠላት ታንክ አላስረክብም ብሎ ታንኩን ማሽከርከር ተያያዘ። በድፍረት እና በወኔ እየነዳ የተሻለ ቦታ በመያዝ ከጥሻ ወጣ። በኋላም ዳግም ጥቃት ጀመረ። ደብረዘቢጥ እና ገረገራ በቁጥጥር ሲውሉ በዚችው ታንክ ድል በማድረግ ውጊያውን በጀግንነት ተውጥቷል።

የአስር አለቃ አብርሃምና የታንኳ ታሪክ በጋሸና ግንባርም ተደግሟል። በአካባቢው በተደረገ ከባድ ውጊያ ላይ የታንኩ የኋለኛው ሰንሰለት ቸርኬ ተመቶ ይወልቅበታል።ይህንኑ በመረዳቱም ለቡድን አጋሮቹ የመድፍ ጥይቶችን እንዲተኩሱ የሚያስችል አቅጣጫ በመያዝ ተኳሾቹ በወዲያኛው ማዶ ያለውን ጥቃት መከላከል የሚያስችል ከባድ ምት እንዲያሳርፉ አደረገ። በኋላም የኋላ ቸርኬ ሰንሰለት ማሽከርከሪያው የተመታውን ታንክ የመንተት ያህል እየነዳ ወደነጻ ቀጠና በማድረስ ታላቅ ጀብድ በታንኳ ፈፅሟል።

ኢትዮጵያ ምንም እንኳን በራሷ ጉያ ተወሽቀው ሳቋን እየቀሙ ውርደቷን የሚያፋጥኑና መበተኗን ገሃድ ለማውጣት ሌት ተቀን የሚሯሯጡ ወጪት ሰባሪዎች ቅዠታሞች ቢኖሩትም ክብሯን የሚያስጠብቁ፣ ከራሳቸው ሕይወት ይልቅ የሀገራችውን ክብር


ምክትል መቶ አለቃ ኤርሚያስ ማቲዎስ


ምክትል አስራ አለቃ ገበያነሽ ደባልቄ


አስር አለቃ ጌታቸው ገዛኸኝ

የሚያስቀድሙ፣ የማይታመን ጀግንነት የሚፈፅሙ አስር አለቃ ገበያነሽን የመሰሉ በርካታ የቁርጥ ቀን ጀግኖች አሏት።

ይህ የጀብድ ታሪክ የእነ አስር አለቃ ጌታቸው ገዛኸኝ፣ ምክትል መቶ አለቃ ኤርሚያስ ማቲዎስ፣ አስር አለቃ ገበያነሽ ደባልቄና የአስር አለቃ አብርሃም ብቻ አይደለም።የብዙ ወጣት የመከላከያ ሰራዊት አባላት ጀብድ እንጂ!

አዎ! በየአውደ ግምባሩ በፊትም፤ አሁንም በርካታ ወጣቶች ለሀገራቸው ሉዓላዊነት ሲሉ ታላላቅ ጀብዶችን እየፈፀሙ ይገኛሉ።እነርሱ መስዋት ሆነው ትውልድ በማስቀጠል ደማቅ ታሪክም እየፃፉ ነው።በትውልድ ቅብብሎሽ ዛሬ የተረከቧት ይች ታላቅ ሀገር ዝናዋና ክብሯ ተጠብቆ ለመጪው ትውልድ እንድትሻገር ዛሬም መስዋት እየሆኑ ነው።ለዚህ ጀብዳቸው ደግሞ ታሪክ ሁሌም ይዘክራቸዋል።ዘላለማዊ ክብርና ሞገስ ስለኢትዮጵያ ብለው ሲፋለሙ ላለፉ ወጣቶች!!

# የምድር በረከት

## ባለሀብቶችን ማበረታታትና መሳብን ያለመው የማዕድን ኢንቨስትመንት ልማት ንቅናቄ

**ስምስም መንግሥቱ**

የአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ «ማዕድን አዲስ የንጋት ተስፋ ለክልላችን» በሚል መሪ ቃል ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በባህርዳር ከተማ በቅርቡ የማዕድን ኢንቨስትመንት ልማት ንቅናቄ አካሂዷል። በንቅናቄውም በተለያየ በማዕድን ልማት ዘርፍ የተሰማሩ አካላት ተሳትፈዋል። የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከ ዑማና የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳደር ዶክተር ይልቃል ከፋለን ጨምሮ ዘርፉን የሚመሩ አካላት ተገኝተውበታል፡ በኮቪድ 19 ቫይረስ ወረርሽኝና በሰሜን ኢትዮጵያ በተከሰተውና አሸባሪው ሕወሓት በአማራ ክልል ላይ በፈጸመው ወረራ ምክንያት ይህን መሰል መድረኮችና ንቅናቄዎች ረዘም ላሉ ጊዜያት ሳይካሄዱ ቆይተዋል፤ ይህም ዘርፉ ይበልጥ እንዲቀዛቀዝ ምክንያቶ ሆኖ ቆይቷል።

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በተካሄደው ጦርነት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከዘርፉ ተጠቃሚ የነበረውን፣ ለአገር ኢኮኖሚ እድገት የበኩሉን አስተዋጽኦ በማበርከት ሚና በነበረው የማዕድን ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ጫና ከፍተኛ ነው። በተለይ ደግሞ በአማራ ክልል ዋና ዋና የሚባሉ የማዕድን ሀብቶች መገኛ ስፍራዎች በጦርነት ቀጠና ውስጥ መሆናቸው ችግሩን የከፋ አድርጎታል።

ይህን የተቀዛቀዘውን የማዕድን ልማት በማነቃቃት እንደ አገር በተለያየ ዘርፍ በመንቀሳቀስ ጠንካራ ኢኮኖሚ በመገንባት የማትበገር ኢትዮጵያን ለመፍጠር እየተደረገ ባለው ጥረት አገሪቱ ያላትን እምቅ የማዕድን ሀብት እንዲህ ባሉ የንቅናቄ መድረኮች ጥቅም ላይ እንዲውሉ ማድረግ ይገባል። መድረኩ በዘርፉ በመሥራት ላይ የሚገኙትን ለማበረታታት አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችንም ለመሳብ አማራጭ መፍትሄም ነው።

በማዕድን ኢንቨስትመንት ልማት ንቅናቄ መድረኩ ላይ ለኢንዱስትሪና ለግንባታው ዘርፍ እንዲሁም ለጌጣጌጥ የሚውሉ የማዕድን አይነቶች ለእይታና ለአዳዲስ ኢንቨስትመንት መሳቢያ ቀርበዋል፤ የውይይት መድረክም ባካተተው በዚህ መርሀ ግብር ላይ ዘርፉ በአገር የኢኮኖሚ እድገት ላይ የተሻለ ውጤት እንዲያስመዘግብ የሚረዱ አስተያየቶች ተንሸራሸረውበታል። በዚህም በዘርፉ የተከናወኑ በጎ ሥራዎችና በክፍተት የተለያዩ ሀሳቦች ተነስተዋል።

ከተነሱት ሀሳቦች መካከል በህገወጥ ማዕድን አዘዋዋሪዎች የሚፈፀመው የግብይት ችግር ዛሬም የዘርፉ ማነቆ ሆኖ መቀጠሉን የሚያመለክተው አንዱ ሲሆን፣ የቁጥጥርና ክትትል መላላት ለችግሩ ሥር መስደድ ምክንያት መሆኑም ተጠቁሟል።

በክልሉ ከሚገኘው፣ በዋጋው ውድነትም ሆነ ስማቸው በስፋት ከሚነሳው የከበሩ ማዕድናት መካከል የኦፓል ማዕድን ይጠቀሳል። የኦፓል ማዕድን ኢትዮጵያ ውስጥ በአማራ ክልል በተለይ ደላንታ ወረዳ ውስጥ በስፋት ይገኛል። የአካባቢውም መለያ ጭምር ሆኗል።

በመድረኩ ስለዚህ የኦፓል ማእድን ያነሱት የደላንታ ወረዳ ነዋሪ ገቢ በማስገኘት በአገር ኢኮኖሚ እድገት ላይ ላቅ ያለ ሚና ሊኖረው የሚችለው የኦፓል ማዕድን በአካባቢያቸው ቢኖርም ማዕድኑ እንኳን የአገር ኢኮኖሚን ሊያሳድግ ቀርቶ በቅርበት የሚኖረውንም ማህበረሰብ ኑሮ እየለወጠ አይደለም ሲሉ በቁጭት አስገንዝበዋል። ለዚህም ምክንያቱ በህገወጥ ማዕድን አዘዋዋሪዎች የሚፈፀመው ግብይት፣ ህገወጥነትን ለመከላከልም ጠንካራ የሆነ የአሰራር ሥርአት አለመዘርጋት መሆኑን ይጠቅሳሉ።

በግለሰቡና በሌሎች የመድረኩ ተሳታፊዎች በተመሳሳይ የተነሳው ቅሬታ፣ ቁጭትና ተቆርቋሪነት የተለመደ ነው። በህገወጥ ተግባር ላይ ለተሰማሩት ማበረታቸው የተደረገላቸው እስኪመስል ድረስ ነው ችግሩ የዘለቀው።

ህይወታቸውን እየሰጡ ከአፈር ጋር ታግለው የሚያለሙ ግለሰቦችና ማህበራትን ቅሬታ ለምን መፍታት አልተቻለም ? የሚለው ዛሬም ድረስ የመወያያ አጀንዳ ሆኖ መቀጠሉን በንቅናቄ መድረኩ የቀረቡ አስተያየቶች ማሳያ ናቸው።

በመድረኩ ተሳታፊዎች ስለተነሱት ሀሳቦችና አጠቃላይ የንቅናቄ መርሃግብሩን በተመለከተ ማብራሪያ የሰጡን የአማራ ክልል ማዕድን ሀብት ቢሮ ኃላፊ አቶ ኃይሌ አበበ፤ በመድረኩ ኦፓል ማዕድን በህገወጥ መንገድ ከአገር እየወጣ ነው። ይህንንም እያደረጉ ያሉት በዘርፉ የተሰማሩ ቻይናውያንና ህንዳውያን ናቸው። ይህም የሆነው መንግሥት ለዘርፉ ተገቢውን ትኩረት ሳይሰጥ በመቅረቱ ነው። በቀጣይ ምን ለመሥራት አስባችኋል? የሚል ጥያቄና አስተያየት እንዲሁም ከቀረጥ ነጻ የኢንቨስትመንት ማበረታቻ፣ ከመሰረተ ልማት ማሟላት ጋር የሚያያዙ ሌሎች ልማቱን ሊያበረታቱ የሚችሉ ሀሳቦች መነሳታቸውን ይጠቅሳሉ።



በማዕድን ኢንቨስትመንት ልማት ንቅናቄ መድረኩ የክልሉን እምቅ የማእድን ሀብት ማስተዋወቅ ተችሏል

አቶ ኃይሌ እንዳሉት፣ የተነሱት አስተያየቶች አግባብነት አላቸው። ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ኦፓል ማዕድን በዓለምአቀፍ ደረጃ የሚታወቅ (ብራንድ) ነው። ሆኖም ግን ዘርፉ ለህገወጥ ተጋላጭ መሆኑ የአገርን ጥቅም አሳጥቷል።

ባለፈው በጀት ዓመት ክልሉ ከኦፓል ልማት ወደ ሰባት ሚሊየን ዶላር ገቢ አስገኝቷል። በክልሉ ከሚገኘው የማእድን ሀብት ክምችት መጠን አኳያ ከዚህም በላይ ገቢ ማስገኘት ይጠበቃል። እንዲህ ያለውን ክፍተት ለመሙላት እንደሚገባ በክልልም በአገር ደረጃም ትኩረት የተሰጠው ጉዳይ ነው።

ዘርፉ በመዋቅር እንዲታገዝ ማድረግ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ከተደረጉ ጥረቶች መካከል ይጠቀሳል። ወረዳዎች በቅርብ ክትትልና ድጋፍ እንዲያደርጉ የአሰራር ሥርአት ተዘርግቷል። ሥርአቱ ህገወጥነትን ለመከላከል አንዱ መፍትሄ ተደርጎ ይወሰዳል። በዞን፣በወረዳ በክልል ደረጃ በየመዋቅሩ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደረግ የፀጥታ ኃይልን ያሳተፈ ግብረኃይል ተቋቁሟል። ግብረ ኃይሉን ማጠናከር ያስፈልጋል። በተጨማሪም በተመረጡ ወረዳዎች የማዕድን መገበያያ ማእከሎች መኖር አለባቸው። ይህንንም ተፈጻሚ ለማድረግም እንቅስቃሴ ተጀምሯል።

የንቅናቄ መርሃግብሩ የወደፊት ስኬቶችን ታሳቢ ባደረገ ኢንቨስትመንትን ማጠናከር እንዲሁም በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል የተከፈተውን ጦርነት ከመመከት ጎን ለጎን የልማት ሥራውን ማጠናከርን ታሳቢ ያደረገ ነው። በግብርናው እና በሌሎችም የልማት ዘርፎች እንደ አገር ስኬት ለማስመዝገብ ጥረት እንደሚደረገው ሁሉ የማዕድን ልማቱም በክፍለ ኢኮኖሚው ላይ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት በተመሳሳይ በትኩረት እንዲሰራ ባለድርሻውን በማነቃቃት እየተሰራ ነው።

በክልሉ ስለሚገኙ እምቅ የማዕድን ሀብቶች፣ ዘርፉ ጥቅም ላይ ቢውል ሊያስገኝ ስለሚችለው ጠቀሜታ ግንዛቤ መፍጠር፣ በዘርፉ ላይ ስለሚስተዋሉ ተግዳሮቶችና ስላለው ምቹ ሁኔታ እንዲሁም ተግዳሮቶችን እንዴት መቅረፍ እንደሚቻልና በጎ ጎኑን ለማጎልበት ደግሞ ወደፊት መከናወን ስላለባቸው ተግባራት የተዳሰሰበት መርሃግብር መሆኑን ሃላፊው አብራርተዋል።

በክልሉ ለኢንዱስትሪ፣ ለግንባታና ለጌጣጌጥ ግብአት የሚውሉ በአምስት ዘርፍ የተከፈሉ 40 የሚደርሱ የማዕድን አይነቶች በጥናት ተለይተዋል የሚሉት የቢሮ ሃላፊው፣ከነዚህ ውስጥም ለአብነት ከፍተኛ ክምችት ያለው ለመኪና ባትሪ ግብአት የሚውል ሊቲየም የተባለ ማዕድን በወሎ አካባቢ እንደሚገኝ ጠቁመዋል። አንድ ቶን ሊቲየም ጥሬ ማዕድን አሁን ባለው ዓለምአቀፍ ገበያ 17ሺ ዶላር ዋጋ አለው ሲሉም ነው ያብራሩት።

ለአውሮፕላን መስሪያ የሚውል ኮባልት የተባለ ማዕድንም በክልሉ እንደሚገኝም አስታውቀው፣ አንድ ቶን ኮባልት ጥሬ ማዕድን 51ሺ ዶላር ይሸጣል ብለዋል። እንዲህ ለተለያየ ግብአት የሚውል ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ያለው ማእድን እንዳለም ነው የጠቀሱት። በዘርፉ ያለውን ዓለምአቀፍና የአገር ውስጥ የገበያ ሁኔታ እንዲሁም የማዕድን መገኛዎችን አለመገንዘብ እንደሚስተዋልም ይጠቅሳሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ የንቅናቄ መርሃግብሩ እንዲህ ያሉ ክፍተቶችን ለመቅረፍ ከማስቻሉ በተጨማሪ በክልሉ የሚገኙ ማዕድናትን አይነትና የሚገኙባቸውን አካባቢዎች በማስተዋወቅ ኢንቨስትመንት ለመሳብ ጥረት የተደረገበት ነው። ኤግዚቢሽንና ውይይትን በጋራ በማቀናጀት የተካሄደው የንቅናቄ መድረክ በዘርፉ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን ከመዳሰሱ በተጨማሪ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግሥት ለዘርፉ የሰጠው ትኩረት የተመሰገነበትና ቀጣይነት እንዲኖረው መልእክት የተላለፈበት በመሆኑ ዓላማውን ያሳካ ሆኖ ተገኝቷል።

በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በተካሄደው ጦርነት አንዳንድ የክልሉ አካባቢዎች በጦርነት ቀጣና ውስጥ መገኘታቸው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በዘርፉ ላይ ተጽእኖ ማሳደሩ አይቀርም። ኢንቨስትመንትን ለመሳብ ታሳቢ ባደረገው ንቅናቄ ላይ የተጽዕኖው ስጋት በተመሳሳይ ይኖር እንደሆን አቶ ኃይሌ ለቀረበላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽ፤ አብዛኞቹ የማዕድን መገኛዎች ከጦርነት ቀጠና ውጭ በመሆናቸው ስጋት አይሆንም ብለዋል። ለአብነት የሲሚንቶ ፋብሪካ መገንባት የሚፈልግ ባለሀብት አባይ ሸለቆ ላይ፣ ድንጋይ ከሰል ላይ መሰማራት የሚፈልግ ጭልጋ፣ አምባሰል፣ ደብረኤልያስ፣ አንኮበር አካባቢዎች፣ የወርቅ ማዕድን ደግሞ ወበርማ አካባቢ ይገኛሉ።

እነዚህ አካባቢዎች በንቅናቄ መድረኩ ላይ በመጠቆማቸው ከመድረኩ ተሳታፊዎች ብዙዎች ፍላጎት አሳይተዋል። በተለይ በድንጋይ ከሰል ልማት ላይ የኢንቨስትመንት ጥያቄዎች ቀርበዋል። ጭልጋ አካባቢ ወደ ሶስት ነጥብ ዘጠኝ ሚሊየን ቶን የሚሆን የድንጋይ ከሰል ክምችት እንደሚገኝ በጥናት ተለይቷል። በድንጋይ ከሰል ልማት ላይ ብዛት ላላቸው አልሚዎች ፍቃድ የተሰጠ ሲሆን፣ ከነዚህም አምባሰል አካባቢ በአምስት መቶ ስልሳ አምስት ሚሊየን ዶላር ወጭ ግንባታ ለማካሄድ አንድ አልሚ በእንቅስቃሴ ላይ ይገኛል።

በአገር ውስጥ ባለ ጥሬ ዕቃ በመጠቀም ከውጭ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚገባውን የድንጋይ ከሰል መተካት እንደሚገባ በመንግሥት የተያዘው አቅጣጫ በተለያየ የማዕድን ዘርፍ የተሰማራውን ያበረታታል ያሉት አቶ ኃይሌ፤ ለግንባታ ዘርፍና ለሲሚንቶ አምራች ኢንዱስትሪዎች ግብአት በሚውለው የድንጋይ ከሰል ልማት ላይ የተጀመረውን እንቅስቃሴም ለአብነት አንስተዋል።

የባለሙያም ሆነ የቢሮ አደረጃጀት የማዕድን ልማቱ በሚከናወንባቸው ገጠራማው አካባቢዎች ጠንካራ መሆን ሲገባው ምቹ ሁኔታ የተፈጠረው ሥራውን ለሚቆጣጠረው ከፍተኛ አመራሩ ነው በሚል በአንዳንድ የምጣኔ ሀብት ባለሙያዎች ስለሚቀርቡ ትችቶች የተጠየቁት አቶ ኃይሌ በሰጡት ምላሽ «በማዕድን ዘርፍ ላይ ይስተዋሉ የነበሩ ክፍተቶች ከፖሊሲ እንደሚጀምሩ ይናገራሉ። ይህ ደግሞ ለዘርፉ ያለው አመለካከት ዝቅ እንዲል አድርጎታል ነው የሚሉት። እሳቸው እንዳሉት፤ ስራው በፖሊሲ ካልታገዘ ተቋም መገንባት አይቻልም።ለአብነትም የአማራ ክልልን ማንሳት ይቻላል። ዘርፉ አንዴ በግብርና ሌላ ጊዜ ደግሞ ውሃን በተመለከተ በሚመራው አካልና በሌላም ተቋም ሥር እንዲሰራ ሲደረግ ነው የቆየው። ዞንና ወረዳ ላይ ደግሞ መዋቅር የለውም። ማዕድን የብልጽግና መንገዳችን ነው ብሎ ከማሰብ ይልቅ ማዕድንን የግጭትና የፀብ መነሻ አድርጎ የመውሰዱ ሁኔታ ነበር ጎልቶ ይታያል። በዚህ የተነሳ ከላይ እስከታች ባለው አመራር ትኩረት አላገኘም።

አሁን ላይ ግን አሰራሩ ተለውጧል፤ ከአገራዊ ለውጡ በኋላ ሥራዎችና አደረጃጀቶች መለወጣቸውን፣ ክልሉ ማዕድን ኤጀንሲ የነበረው በቢሮ ደረጃ በማደራጀት የካቢኔ መዋቅር ውስጥ እንዲገባ ማድረጉን፣ ዞኖች ላይም በተመሳሳይ የካቢኔ አካል በማድረግ ወደ መምሪያ መቀየሩን፣ ወረዳ ላይ ደግሞ በተመረጡ ወረዳዎች የማዕድን ጽህፈት ቤት ሆነው እንዲያገለግሉ በማደራጀት በትኩረት እየተሰራ ነው ሲሉ አስረድተዋል።

አቶ ኃይሌ በአዲስ አደረጃጀት የተጀመረውን እንቅስቃሴ በማጠናከር ውጤታማ ለመሆን ያልተቋረጠ ሥራ ይሰራል ብለዋል። የንቅናቄ መድረኩም በተለያየ ይዘት የሚቀጥል መሆኑንና በአገር ደረጃ ከህዳር አንድ ጀምሮ የሚካሄደውን ዓለምአቀፍ የማዕድንና ቴክኖሎጂ መሠረት በማድረግ በባህርዳር ከተማ በተመሳሳይ ከህዳር 10 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ እንደሚካሄድ አመልክተዋል።

በማዕድን ኢንቨስትመንት ንቅናቄ መድረኩ ላይ የተገኙት የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ታከለ ዑማ፤ «ኢትዮጵያ በማዕድን ዘርፍ ልታድግና ልትበለጽግ የምትችለው በአገሪቱ ያለው ማዕድን የኢትዮጵያ ነው ብለን ስናምን ነው»ሲሉ አስገንዝበዋል።

የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ በበኩላቸው፤ የአሰራር ማነቆዎችን በመፍታት ለማዕድን ልማቱ መፋጠን ክልሉ የሚችለውን ሁሉ ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ መሆኑን አረጋግጠዋል። በክልሉ ያለውን የማዕድን ሀብት ወደ ልማት ለመቀየር ባለሀብቶች መዋለነዋያቸውን በዘርፉ ላይ እንዲያውሉም ጥሪ አቅርበዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## ውቃቢ ሲርቅ...

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

የምትፋጀውን ጸሀይ ለመሸሽ ስል ለረጅም ሰዐት ከቤት አልወጣሁም ነበር።ከሰዐት ወደ አመሻሽ ሲሳብ ቀን ሙሉ ካላየሁት ደጅ ጋር ተያየሁ።የጸሀይዋን ማረጥ ተከትዬ ብቻዬን ስሆን የምተክዘውን ትካዜ እየተከዝኩ ወደ አንድ ሄጄበት ወደማላውቀው ሰፈር አመራሁ።ትካዜ አቅል እንደሚያሳጣ ዛሬ ነው ያወኩት።ለብዙ ዘመን ተክዤ አውቃለው እንደዛሬው ግን ከማላውቀው ሰፈር ከማላውቃት ሴት ጋር አገናኝቶኝ አያውቅም።አንዴ ብቻ ነው ያየኋት..አልደገምኳትም..አልሰለስኳትም።በአንድ ጊዜ እይታ ብቻ ግን ለዘላለም ያየኋት ያክል ሲሰማኝ ነበር።ገጽዋ እሳታማ ነው..ከቤት እንዳልወጣ እንደከለከለችኝ የሰባት ሰዐት ጸሀይ።ጠይም ሆኖ እንደ ጸሀይ መድመቅ እንዴት ይቻላል? ሀሳብ ሰለበኝ።

አንድ ጊዜ አየኋት..ከአፍታ ላነሰ፣ ከላመል ለተቆረሰ ጊዜ።አንድ ጊዜ ብቻ ነው ያስተዋልኳት..ከቅጽበት ለጎደለ.. ከኢምንት ለተገመሰ ጊዜ..በዚህ ሁሉ ውስጥ ግን ምኗም ሳይቀር በትካዜ በራደ አእምሮዬ ውስጥ ተቀርጾ ነበር።

ሁለት አይነት ሴት ናት..እየሳቀች የምትጸሙን።በአንድ ጊዜ ሁለት ነፍሷን አየሁት..አንዴ ሳቅ አንዴ ደግሞ ዝም ብላ።ዝምታና ሳቋን በአንድ ጊዜ አየሁት።የመጀመሪያው.. ከእሷ ውበት መለስ ካለች እንደ አስፓልት ከጠየመች ጓደኛዋ ጋር ታክሲ እየጠበቁ ቆመዋል።አጠያየማቸው አንድ አይነት ነው..።ምን እንደሆነ ባልደረስኩበት ለሁልጊዜ በሚናፍቀኝ ወሬዋ ጓደኛዋን እያወራች በራሷ ወሬ የኮረኮሯት ያክል እየሳቀች አየኋት።በራስ ወሬ እንዲህ እንደሚሳቅ አላውቅም ነበር።ወሬኛው እኔ እንኳን በወሬዬ ስንቶችን ሳስቅ በራሴ ወሬ ፈገግ ብዬ እንኳን አላውቅም።ሳቋ ውብ ዜማ ሆኖኝ ውስጤ ተቀመጠ።ትካዜዬ በሳቋ ደንግጦ ላይመለስ ጥሎኝ ጠፋ።ከዛሬ በኋላ መቼም የምተክዝ አይመስለኝም.. ሳቋ ለዘላለም የተሸከምኩትን የእናቴን ውቃቢ ከላዬ ላይ ያባረረልኝ ይመስለኛል።ሁለተኛው..ይሄን ሳቋን ያጸለመችበት ምዕራፍ ነው።ሰው እንደዛ ስቆ እንደዛ ዝም ይላል? በሳቅ የፈካ ፊቷን ከየት እንዳመጣችው ባልደረስኩበት ጽሞና ሞላችው።ብዙ ነገሯ ገረመኝ..ውበቷ፣ በአንድ ጊዜ ከሳቅ ወደ ዝምታ ያደረገችው መመለስ።ተጠራጠርኳት.. እንደ እኔ በትካዜ መሄጃ ያጡ ነፍሶችን ለመታደግ ሰው የሆነች መሰለኝ..ደግሞም አመንኳት..ልቤ ግን በዚች ሴት እንግዳ ሀሳብ ተጠምዳ ነበር።

የሆነ ለዘላለም የምረግመው ገላው ላይ የጃማይካዊው የቦምማርሌ ስዕል ያለበት ሰማያዊ ታክሲ መጥቶ ይዟት እስከተሰወረ ጊዜ ድረስ በዛ ቦታ ስለ እሷ እያሰብኩ ተገትሬ ነበር።እሷን በጫነው ታክሲ ቀናሁ።አብረዋት በተሳፈሩ መንገደኞች፣ አብሯት በተቀመጠው ሰው ቀናሁ።በሾፌሩ.. ከእሷ እጅ ላይ ሂሳብ በሚቀበለው ወያላ ቀናሁ።በዝምታና ሳቋ ተለክፌ ወደ ቤቴ ተመለስኩ።ያን ዝምታና ሳቅ በልቤ ሳሎን ላይ ሰቅዬ ለዘላለም አስታውሰዋለው።ይሄ ከዛ ቦታ ስሸሽ ለራሴ የገባሁት የማይታጠፍ ቃል ኪዳን ነበር።

አንዳንድ ቀኖች እንዲህ ናቸው..ወይ ከህይወት ያጎላሉ ወይ ጎደሎ ይሞላሉ።የእኔ እጣ ፈንታ ምን እንደሆነ አልደረስኩበትም።ቤት ስደርስ ሚስቴ አስጠላችኝ።በዛ ፈገግታ..በዛ ጽሞና በማንም እንደማልተካው ያወራሁለት የሚስቴ ፈገግታና ዝምታ አስጠላኝ።ለአፍታ ባየኋት ሴት ውበትና ፈገግታ ተረትቼ ለዘመናት የገነባሁትን ትዳሬን ገፋሁት።ሚስቴ እንደ እሷ እንድትስቅ፣ በአንድ ጊዜ ብዙ አይነት ሴት እንድትሆን ብዙ ለፋሁ አልሆነም።በሚስቴ ሴትነት ውስጥ ያቺን ለአንድ ጊዜ ያየኋትን ሳቂታ ሴት ፈለኳት አላገኘኋትም።በእንግዳ ባህሪዬ እኔም ሚስቴም ተቸገርን።ራሴን እንደ ድሮው መፍጠር ግን አልቻልኩም።ወደ ትካዜዬ ተመለስኩ..ዳግመኛ ይጎበኛል ብዬ ወዳላሰብኩት ትካዜዬ ዳግመኛ ላልወጣበት ተዘፈኩበት።በትካዜዬ ውስጥ እንደ ድሮው እናቴ ብቻ አልነበረችም እናቴን የማትመስል ሌላም አንዲት ሳቂታ ሴት ነበረችበት።

ትካዜ የአእምሮ መሞት ነው..የልብ መሰለብ ነው።ትካዜ ነፍስ ከስጋ ጋር ስትኳረፍ ዝም የምትለው ዝምታ ነው።ስጋ ከነፍስ ጋር ሲቃየም የሚደብተው ድባቴ ነው።ሰው ከተከዘ ከሙላቱ እየጎደለ ነው።ከስፋቱ እያነሰ ነው።የእኔ ትካዜ ግን ይሄን ሁሉ አልነበረም በልጅነቴ ያጣኋት እናቴ በሀሳቤ ውስጥ እየተሰነቀረች የምተክዘው ትካዜና ዝም የምለው ዝምታ ነው።ችግሮቼን አምኜ ስለማልቀበል ይሆን እንጃ እንደዛ ነው የሚመስለኝ።

በልጅነቴ ውቃቢ ሲርቀኝ የኖርኩ ልጅ ነኝ።ዛሬም በልጅነቴ ከማውቀው ውቃቢ ጋር ተገናኝቻለው።እናቴ በልጅነቴ ያልተገባ ነገር ሳደርግ ‹ምነው ውቃቢ ራቀህ? ትለኛለች።እኔን ብቻ አይደለም ቤቱ ውስጥ ያለውን ሁሉ በዚህ ንግግሯ ነው የምትቀበለው።ግራ በገባት አንድ ቀን ላይ ራሷንም ‹ምነው አሁንስ ውቃቢ ራቀኝ ብላ ታውቃለች።ውቃቢ ምን እንደሆነ አላውቅም ብቻ በዛ የልጅነት ጭንቅላቴ ከእናቴ ንግግር ተነስቼ ውቃቢ ማለት የፈጣሪ ሌላኛው ስሙ ይመስለኝ ነበር።እና ደግሞ ለፈጣሪ የቀረበ..እምነት የሚጣልበት ሌላ ሀይል ይመስለኛል።ከእናቴ ንግግር ተነስቼ ሁለት አምላክ ያለ ይመስለኝ ነበር።እናቴ አንድም ቀን ‹ምነው እግዚአብሄር ራቀህ..ወይም ደግሞ ምነው መላኩ ራቀህ ብላኝ አታውቅም።እንከኖቼ ሁሉ ከማላውቀው ውቃቢ ጋር የተያያዙ ነበሩ።በዚህም ሁለት አምላክ እንዳለ ይሰማኝ ነበር።ዛሬም ያልተገባ ነገር ሳደርግ ራሴን ‹ምነው ውቃቢ ራቀኝ እላለው..ውቃቢ ምን እንደሆነ ግን አላውቅም።

ውቃቢ ርቆኛል..በትካዜዬ ውስጥ ወደማላውቀው ቦታ ሄጄ በማላውቃት ሴት የተፈጠረ ውቃቢ።እናቴ ልክ ነበረች? ብቻ አላውቅም የማላውቀው ውቃቢ እንደራቀኝ ግን እርግጠኛ ነበርኩ።ሰው እንዴት ለምን እንደተሳቀ በማያውቀው ሳቅ ይረታል? ሰው እንዴት ለአንዴ አይቷት ዳግመኛ በማያገኛት ነፍስ ታሪኩን ያበላሻል? ሰው እንዴት የልጅነት ጠዋቱን በከሰዐት አመሻሹ ይሸሽጋል? ራሴን እንዲህ እጠይቃለው።እውነትም ውቃቢ ርቆኛል።ዳዴ ባልኩበት ጠዋቴ ላይ ያገኘኋትን ሚስቴን ምኑንም በማላውቀው ከሰዐቴ ላይ ማሳዘኔ ከውቃቢ መራቅ በላይ እንደሆነ ደረስኩበት ቢሆንም ግን ሳቂታዋን ሴት መርሳት አልቻልኩም።

ህይወት የፈታይ ቀሰም ናት..ፈትል የተጠመጠመባትና የሚጠመጠምባት።እናም የምንኖረው በህይወት ቀሰም ላይ ለመጠምጠምና የተጠመጠመን ለመፍታት ነው።ሳናውቃቸው የሚመጡ መጥተውም የማይደገሙ የህይወት አንድ ጊዜዎች አሉ።ልክ ሳቂታዋን ሴት እንዳየሁበት ደግመን የማንስቅባቸውና ደግመን የማንተክዝባቸው አንድ ጊዜዎች።አለም ላይ ምን ይደገምልህ ቢባል ያቺን እሷን ያየሁባትን ቅጽበት እል ነበር። ምን ይናፍቅሀል? ላለኝ እሷን ያየሁባትን አፍታ ስል ደግሜ ደጋግሜ የምመልሰው መልስ ነበረኝ።አይኖቼ ሰላሳ ስምንት አመት ሲያስተውሉ የእሷን መሳይ ውበት አላስተዋሉም ነበር።አእምሮዬ ለአርባ አመት ለቀረበ ዘመን ሲተክዝ የእሷን መሳይ ትካዜ አላስተናገደም ነበር።የእሷን መሳይ መገረም አልጎበኘውም ነበር።

በዛች እንደ ሀምሌ ሰማይ በጠየመች ሴት መልክ የሚስቴ ቀይ ዳማ መልክ አስጠላኝ።በከለሯ እንዳልጎመጀሁ ሚስቴ ጠይም እንድትሆንልኝ መሻት ጀመርኩ።በመልካሟ ሚስቴ ላይ ሸፈትኩ።ጨከንኩባት።ምን ያክል ራስ ወዳድ እንደሆንኩ የተሰማኝ..ከምንምነት አንስታ ሰው ያደረገችኝን መልካሟን ሚስቴን ምኗንም በማላውቃት ሴት ለመቀየር የተነሳሁ ቀን ነበር።እንደዛም ሆኖ አልተጸጸትኩም..በትካዜዬ ውስጥ ይያት ብዙ ቀን ወደ ጠይሟ ሴት ሰፈር ሄድኩ...ጭራሽ ያልነበረችን ሴት ፍለጋ።ውቃቢ ርቆኝ የለ?

# ዓለም አቀፍ



አይ ኤስ አይ ኤል የሽብር ቡድን አባላት

## የሶማሊያ ሽብርተኞችን ለማዳከም የታለመ አዲሱ የአሜሪካ ማዕቀብ

አሜሪካ በሶማሊያ ሕገ ወጥ የጦር መሣሪያ ዝውውር ላይ የተሰማሩ ሽብርተኛው አይ ኤስ አይ ኤል የኢስላማዊው ቡድን አባላት ላይ ያነጣጠረ አዲስ ማዕቀብ መጣሏን አስታወቀች።

ማዕቀቡ የቡድኑ በአፍሪካ ለሽብር የሚጠቀመውን የገንዘብ ዝውውር መረብ ለመበጠስ እንደሚረዳም ተገልጿል።

ዩናይትድ ስቴትስ በሶማሊያ አይ ኤስ አይ ኤል የቡድኑ አባላትና ሌሎች ላይ ያነጣጠረ ማዕቀብ የጣለችው ማክሰኞ እለት ሲሆን እርምጃው በምስራቅ አፍሪካ "በአሸባሪ የጦር መሳሪያ ማዘዋወር መረብ" ተሳትፎ በማድረጋቸው ምክንያት መሆኑም ተነግሯል።

የአሜሪካ ስቴት ዲፓርትመንት የግምጃ ቤት ባለሥልጣናት ጦር መሣሪያን በሕገ ወጥ መንገድ ያዘዋወሩት አሊያም የአልሸባብ ቀንደኛ አባላት የነበሩ ግለሰቦች በማዕቀቡ ውስጥ መካተታቸውን ይፋ አድርጓል።

የአይ ኤስ አይ ኤል ሽብር ቡድን ባሳለፍነው ቅዳሜ በሶማሊያ መዲና በሞቃድሾ ለ120 ሰዎች ሕይወት መጥፋት ምክንያት የሆነው የቦምቦች ፍንዳታ ኃላፊነቱን እንደሚቀበል ገልጾ ነበር።ቡድኑ ከአምስት ዓመት በፊት በተመሳሳዩ ቦታ በፈጸመው የቦምብ ጥቃት ከ500 በላይ ሰዎችን መግደሉ ይታወሳል።

ዋሽንግተን በሶማሊያ የሚንቀሳቀሱ ሽብርተኞች መረብ ለመበጣጠስ ከጣለችው ማዕቀብ በተጨማሪ ከቀጣዩ ሳምንት በኋላ ሌላ እርምጃ እንደምትወስድም ተጠቅሷል።

አሜሪካ እ.ኤ.አ በ2018 በሶማሊያ የሚንቀሳቀስ የአይ ኤስ አይ ኤል ቡድን በአለም አቀፍ ሽብርተኝነት መፈረጇ የሚታወስ ሲሆን የአሁኑ ማዕቀብም ከፑንትላንድ ግዛት በርካታ የጦር መሣሪያን በሕገ ወጥ ወደ ሦማሊያ በማስገባት ሀብት ያካበተውና የሽብር ቡድኑ አባል አብዲራህማን መሀመድ አማር፣ እንዲሁም በፑንትላንድ ግዛት የጦር መሣሪያና ሎጀስቲክስ ዝውውር አመቻች ኢሴ መሀሙድ ዩሱፍ፣ የቡድኑ የደህንነትና የመረጃ ክንፍ መሀመድ አህመድ ቃህዬ እና የቡድኑ አሚር የሚባለው አብዲራህማን ፋህዬ ኢሴ መሀሙድ ዒላማ መደረጋቸው ተገልጿል።

## አስደንጋጩ የኮሪያ ምድር ውጥረት

ሁለቱ ኮሪያውያን ከአውዳሚና አሰከፊ ጦርነት በኋላ እ.ኤ.አ በ1948 በመለያየት ሰሜንና ደቡብ ኮሪያ በመባል የየራሳቸው ግዛት ከመሰረቱት ድፍን 74 ዓመታትን አስቆጥረዋል። ሆኖም ግን አልፎ አልፎ በመካከላቸው የሚከሰት ግጭት ሙሉ በሙሉ ለማስቆም እ.ኤ.አ 2018 የሰላም ስምምነት ከተፈራረሙ ወዲህ ሰሞኑ በኮሪያ ምድር የሚታየው ወታደራዊ ድግሶችና የሚሳኤል ጫጫታዎች ድፍን አለምን ያስደነገጠ ክስተት ሆኗል።

አሜሪካ እና ደቡብ ኮሪያ ባሳለፍነው ሰኞ ግዙፍ የአየር ኃይል ወታደራዊ ልምምድ በጋራ ማድረጋቸው ተከትሎ ሰሜን ኮሪያ “ከዚህ በኋላ አልታገዝም” በማለት የረጅም ርቀት ሚሳኤሎችን ሳይቀር ወደ ደቡብ ኮሪያና ጃፓን ምድር እያስወነጨፈች ትገኛለች። በትናትናው እለት ብቻ 23 ሚሳዔሎችን ማስወንጨፏ ተነግሯል።

አሜሪካ እና ደቡብ ኮሪያ የጀመሩት የአየር ኃይል የጋራ ወታደራዊ ልምምድ “ግጭት ቀስቃሽ” ነው ስትልም ሰሜን ኮሪያ ባወጣችው የማስጠንቀቂያ መግለጫ ገልጻለች።

የሰሜን ኮሪያ የማስጠንቀቂያ መልዕክተኞች ከሆኑት ከእነዚህ ሚሳኤሎች አንዱ ደቡብ ኮሪያ የባህር ጠረፍ ከድርንበሯ በ60 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ያረፈ ሲሆን አንድ የአህጉር አቋራጭ ሚሳዔል ደግሞ የኢላማው ስፍራ ሳይደርስ በመሃል ሊወድቅ ይችላል የተባለ ሲሆን፤ በርካታ ጃፓናውያንም ራሳቸውን እንዲጠብቁ እና መከላከያ ምሽጎች ውስጥ እንዲሆኑ የማስጠንቀቂያ መልእክት ደርሷቸዋል ተብሏል።

በተመሳሳይ መልኩ ሰሜን ኮሪያ ደቡብ ኮሪያ እና የአሜሪካ አየር ኃይል የጋራ ወታደራዊ ልምምድ ምላሽ ለመስጠት የታለመ 100 መድፎችን እንደተኮሰችም ተነግሯል።




ሰሜን እና ደቡብ ኮሪያ በቅርቡ በአወዛጋቢው የባህር ድንበር አካባቢ ማስጠንቀቂያ የተኩስ ልውውጥ ማድረጋቸው ተከትሎ በሁለቱም ኮሪያዎች ግጭት ሊፈጠር እንደሚችል ሲዘገብ ቆይቷል።

እስካሁን በሁለቱም ኮሪያዎች መካካል ጦርነት መደረጉ የሚያመላክቱ ሪፖርቶች ባይኖሩም በኮሪያ ባረ ሰላጤ ምዕራባዊ የባሕር ዳርቻ ያለው የባህር ድንበር ለረጅም ጊዜ የዘለቀ ደህንነት ስጋት ምንጭ መሆኑ ተገልጿል።

ከ240 በላይ ዘመናዊ የጦር አውሮፕላኖች የተሳተፉበት የአሜሪካና የደቡብ ኮሪያ የጋራ መታደራዊ ልምምድ የተበሳጨች ሰሜን ኮሪያ የምታደረገው የሚሳኤል ማስጠንቀቂያ ሁለቱን አገራት ዳግም ወደ ጦርነት ይከታል የሚል ትልቅ ስጋት ፈጥሯል።

# ስፖርት





# ተቋርጦ የነበረው የ30 ኪሎ ሜትር ውድድር እሁድ በቢሾፍቱ ይካሄዳል

ብርሃን ፈይሳ

ተቋርጦ የቆየው የ30 ኪሎ ሜትር ጎዳና ላይ ሩጫ ከነገ በስቲያ በቢሾፍቱ ከተማ ይካሄዳል። በዚህ ውድድር ላይም በዓለም አቀፍ ውድድሮች ስኬታማ መሆን የቻሉ ታዋቂ አትሌቶች ተሳታፊ እንደሚሆኑ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አስታውቋል።

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በአዲሱ የውድድር ዓመት የመጀመሪያውን ውድድር ለማካሄድ ዝግጅቱን አጠናቋል። በዚህም መሰረት ከሁለት ዓመታት በላይ ተቋርጦ የቆየውን የ30 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ ዘንድሮ ለ9ኛ ጊዜ ያካሂዳል። በ2012 ዓ.ም ይህንን ውድድር ለማካሄድ ዝግጅት ሲደረግ ቢቆይም በወቅቱ በመላው ዓለም በተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት ሊሰረዝ ችሏል። ባለፈው ዓመት ሊካሄድ ታስቦም ፌዴሬሽኑ በገጠመው የስራ መደራረብ ምክንያት ሊሰረዝ ችሏል።



በውድድሩ ከአራት መቶ በላይ አትሌቶች እንደሚሳተፉ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሰጠው መግለጫ ጠቁሟል፣

ውድድሩን ከነገ በስቲያ በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ቢሾፍቱ ከተማ የሚያካሄድ ሲሆን፣ ሁለት ክልሎች፣ 12 ክለቦች፣ የግል ተወዳዳሪዎች እንዲሁም አንጋፋ አትሌቶች ተካፋይ ይሆኑበታል። ከእነዚህም መካከል በርካታ ታዋቂ አትሌቶች የውድድሩ ተካፋዮች ናቸው። በወንዶች በኩል ሙሌ ዋሲሁን፣ ፋንታሁን ሁነኛ፣ ጠበሉ ዘውዴ፣ ብርሃኑ በቀለ፣ ልመንህ ጌታቸው፣ ኃይለማርያም ኪሮስ እና ባየልኝ ተሻገርን የመሳሰሉ አትሌቶች የውድድሩ ተካፋይ መሆናቸውን አረጋግጠዋል። በሴቶች በኩል ደግሞ ህይወት ገብረኪዳን፣ ሶፊያ ሽምሱ፣ አጸደ ባይሳ፣ ትዕግስት በቀለ፣ ታዱ ተሾመ፣ ባሻንቄ እሙሴ፣ መገርቱ ገመቹ፣ ብሩክ ታምሬ እና ሃገሬ በላቸውም በውድድሩ የሚሳተፉ ታዋቂ አትሌቶች መሆናቸውን ፌዴሬሽኑ ትናንት በሰጠው መግለጫ አሳውቋል።

ዓላማውን ለክልልና ከተማ አስተዳደር ክለብ ተቋማት የግል ተወዳዳሪ አትሌቶች የውድድር ዕድል መፍጠር ያደረገው ውድድሩ፤ አትሌቶች ከውድድሩ በሚያገኙት ሽልማት እንዲበረታቱ የሚያስችልም ነው።

በዚህ ውድድር በአጠቃላይ 404 አትሌቶች የሚካፈሉ ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ 100 የሚሆኑት ሴቶች 304ቱ ደግሞ ወንዶች ናቸው። በዚህም መሰረት የ30 ኪሎ ሜትር ውድድር በሁለቱም ጾታዎች ሲደረግ፤ በአንጋፋ አትሌቶች መካከል የሚካሄደው ውድድር ግን 15 ኪሎ ሜትር የሚሸፍን ነው። የረጅም ርቀት የጎዳና ላይ ውድድር እንደመሆኑ መካፈል የሚችሉት አትሌቶች እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ መሆን እንዳለበትም ተጠቁሟል።

ውድድሩ በታሰበው መልክ እንዲካሄድ የሚያደርጉ ባለሙያዎች እንዲሁም በጎ ፈቃደኞችም ዝግጅታቸውን አጠናቀው ውድድሩ የሚካሄድበትን ቀን በመጠባበቅ ላይ ይገኛሉ። ለአጠቃላይ ለዚህ ውድድርም ፌዴሬሽኑ ከ700ሺ ብር በላይ ወጪ ሲያደርግ ከዚህ ውስጥ ከ318ሺ ብር ለሽልማት የሚውል መሆኑ ታውቋል። በውድድሩ ከአንድ እስከ ሶስት የሚወጡ አትሌቶች እንደየደረጃቸው ከሚያገኙት የሜዳሊያ ሽልማት ባለፈ እስከ ስምንት ባለው ደረጃ ሩጫውን ለሚያጠናቅቁ ደግሞ የገንዘብ ሽልማት የሚበረከትላቸው ይሆናል። በዚህም በሁለቱም ጾታ አሸናፊ የሚሆኑት አትሌቶች የ40ሺ ብር ተሸላሚ ሲሆኑ፤ ሁለተኛ የሚሆኑት 20ሺ እንዲሁም ሶስተኛዎቹ 18ሺ ብር የሚያገኙ ይሆናል።

በተመሳሳይ በአንጋፋ አትሌቶች መካከል በሚካሄደው የ15 ኪሎ ሜትር ሩጫ ከአንድ እስከ ስድስት ባሉት ደረጃ ለሚያጠናቅቁ አትሌቶች የገንዘብ ሽልማት ተዘጋጅቷል። አሸናፊ የሚሆነው 6ሺ ብር፣ ሁለተኛ እና ሶስተኛ የሚሆኑት ደግሞ 3ሺ እና3ሺ ብር ተሸላሚዎች ናቸው።

ይህ የ30 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ ሩጫ ውድድር ለመጀመሪያ ጊዜ በ2001 ዓ.ም በአዳማ ከተማ ነበር የተካሄደው። ለሶስት ተከታታይ ዓመታት ከተካሄደ በኋላም ውድድሩ እስከ 2010 ዓ.ም ተቋርጦ ቆይቷል። ከዓመታት በኋላም አራተኛውንና አምስተኛውን ውድድር በቢሾፍቱ ከተማ መካሄዱን ከፌዴሬሽኑ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል።


## የጨረታ ማስታወቂያ
## የግዥ መለያ ቁጥር 001/ኢዜአ/2015

የኢፌዲሪ ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት በ2015 በጀት አመት (የመኪና ኪራይ አገልግሎት ግዥ በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ሥርዓት (Electronic Government Procurement system) በመጠቀም በብሔራዊ ግልፅ ጨረታ የግዥ ዘዴ አወዳድሮ ግዥ ለመፈጸም ይፈልጋል:: የጨረታው ማስረከቢያ ቀነ ገደብ በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ሥርዓት ድረ-ገጽ www.ppa.gov.et eGP Portal ላይ የሚገለፅ ሲሆን፤ ተጫራቾች ማሟላት የሚጠበቅባቸው ዝርዝር የህጋዊነት ብቃት ማረጋገጫ በሲስተሙ ድረ ገጽ ላይ ይፋ በተደረጉት ዝርዝር የጨረታ ማስታወቂያና የጨረታ ሰነድ ላይ ማግኘት ይችላሉ:: በጨረታው መሳተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች በኤሌክትሮኒክ የመንግስት ግዥ ሥርዓት ድረ-ገጽ www.ppa.gov.et በመግባት EGP Portal ላይ መመዝገብ ይጠበቅባቸዋል። በሲስተሙ ያልተመዘገቡ ዕጩ ተወዳዳሪዎችም ከላይ በተጠቀሰው ድረ-ገጽ ላይ get started የሚለውን በጠቀም የአንድ ጊዜ የምዝገባ ሂደቱን ማከናወን ይችላሉ:: ጨረታው የሚከፈተው በሲስተሙ በቀጥታ (Online) ሲሆን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ለዚሁ ዓላማ ጥቅም እንዲውል በሰነዱ ላይ የተመለከተውን ሊንክ (Link) በመጠቀም በጨረታው አከፋፈት ሂደት ላይ መሳተፍ ይችላሉ:: መስሪያ ቤታችን የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው:: ተጫራቾች ከሲስተሙ በተጨማሪ መረጃ ሲፈልጉ ከዚህ በታች በተጠቀሰው አድራሻ ማግኘት የሚችሉ መሆኑን እንገልጻለን::

**አድራሻ:- አራዳ ክፍለ ከተማ፤ ቸርችል ጎዳና፣ ጥቁር**
**አንበሳ ሆስፒታል ፊትፊት**
**ግዥ ዳይሬክቶሬት, ቢሮ ቁጥር 117**
**ስልክ ቁጥር: +251 812 14 15 / 251 923 63 52 32**
**Email-abdelahusen138@gmail.com**
**የመ.ሣ.ቁ:- 5741**
**አዲስ አበባ, ኢትዮጵያ**

**የኢፌዲሪ ኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት**

## የግልፅ ጨረታ ማስታወቂያ

በልደታ ክፍለ ከተማ ወረዳ 4 ትምህርት ፅ/ቤት ስር የሚገኘው የቀበሌ 37 ቅድመ መደበኛና የአዲስ ፍሬ የመጀ/ደ/ት/ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ዕቃዎች አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል::

ሎት 1፡ የደንብ ልብስ የሰራተኞች ጥቅማጥቅምና የደንብ ልብስ ስፌት የጨረታ ማስከበሪያ ብር 984
ሎት 2፡ አላቂ የቢሮ ዕቃዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 640
ሎት 3 ፡ ለህትመት ስራዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 100
ሎት 4፡ ለአላቂ የትምህርት ዕቃዎች መግዣ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 900
ሎት 5፡ አላቂ ዕቃዎች የፅዳት ዕቃዎች ማስከበሪያ ብር 452
ሎት 6 ፡ ለተለያዩ መሳሪያዎች የጨረታ ማስከበሪያ ብር 300
ሎት 7፡ ለፕላንት ማሽነሪ የጨረታ ማስከበሪያ ብር 600
ሎት 8፡ ለፈርኒቸር/የቢሮ ዕቃዎች/ ማስከበሪያ ብር 300

**ስለሆነም**

1. ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ዘወትር በስራ ሰዓት በአዲስ ፍሬ የመጀ/ደ/ት/ቤት በመቅረብ በማይመለስ ብር 50 /ሀምሳ/መግዛት ይቻላል እንዲሁም ለጥቃቅን እና አነስተኛ ድርጅቶች የድጋፍ ደብዳቤ በማምጣት በነፃ መውሰድ ይችላሉ
2. ተጫራቾች ሀ/ በዘርፉ የታደሰ ንግድ ፍቃድ ያለው/ያላት
ለ/በመንግስት ግዢ ኤጀንሲ በአቅራቢነት የተመዘገበ
ሐ/በተጨማሪ እሴት ታክስ የተመዘገበ ና ቲን ነምበር ማቅረብ የሚችል
3. በየሎቱ በተቀመጠው መሰረት የጨረታ ማስከበሪያ ብር መጠን በሲፒኦ በአዲስ ፍሬ የመጀ/ደ/ት/ቤት በማሰራት ከሰነዱ ጋር ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡
4. ተጫራቾች የሚወዳደሩበትን ዋጋ በጨረታ ሰነድ ውስጥ በሚገኘው የዋጋ ማቅረቢያ ላይ በመሙላት በታሸገ ኢንቨሎፕ ይህ ጨረታ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ባሉት 10 /አስር/ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ በአዲስ ፍሬ የመጀ/ደ/ት/ቤት የጨረታ ሳጥን ውስጥ ማስገባት አለባቸው::
5. ለጨረታ ከቀረቡት እቃዎች ዝርዝር ውስጥ ት/ቤቱ እስከ 20 በመቶ ጨምሮ ወይም ቀንሶ መግዛት መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው
6. የጨረታ አሸናፊ ድርጅት ያሸነፈበትን ንብረት በራሱ ትራንስፖርት የት/ቤቱ ዕቃ ግምጃ ቤት ማቅረብ ይኖርባቸዋል::
7. ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ በወጣ በ10ኛው የስራ ቀን 8፡00 ሰዓት ተዘግቶ የጨረታው ሳጥን በዕለቱ በ8፡30 ሰዓት ላይ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በት/ቤቱ መምህራን ማረፊያ ይከፈታል፡
የጨረታው ቀን መዝጊያና መክፈቻ ቀን ካልሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ከላይ በተጠቀሰው ተመሳሳይ ሰዓት ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈት
8. ተጫራቾች ጨረታው ከመከፈቱ በፊት ለሚወዳደሩበትና ናሙና ለሚያቀርቡባቸው የዕቃ ዓይነት ከመስሪያ ቤታቸው በቀረበው እስፔስፊኬሽን መሰረት ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡
9. ት/ቤቱ የተሻለ መንገድ ካገኘ ጨረታውን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል መሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

አድራሻ፡- የአዲስ ፍሬ የመጀ/ደ/ት/ቤት 5ኛ ፖሊስ ጣቢያ ወረድ ብሎ ልዩ ስሙ ሰላሌ ወፍጮ ቤት ገባ ብሎ
ለተጨማሪ መረጃ ስልክ ቁጥር 0115 51-58-61 /0118-68-56-98

**በአዲስ አበባ ከተማ ትምህርት ቢሮ በልደታ ክ/ከተማ ወረዳ 09**
**ት/ጽ/ቤት የአዲስ ፍሬ የመጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት**